# የእባቡ ዘር

አምላክ ሆይ፡ ሁሉን በመንፈስህ ኃይል የሠራህ፡ ታላቅ እና ገናና አምላክ ነህ፡ ጻድቁን ለእኛ ለኃጢአተኞች፡ በነጻ ይሞት ዘንድ፡ ወደ አገኘነው አስደናቂ የእግዚአብሔር ሕብረት፡ ያስታርቀን ዘንድ፡ አንዲያ ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን የላክህልን ታላቅና ኃያል አምላክ ሆይ፡ ከቅዱስ ቃል እንደተማርነው ዓለም ሳይፈጠር በፊት ከአንተ ዘንድ ሕብረት እንደነበረን ነውና፡ "ያኔ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ አጥቢያ ከዋክብት በአንድነት ሲዘምሩ፡ የእግዚአብሔርም ልጆች ሁሉ እልል ሲሉ።" እግዚአብሔር በታላቅ አሳቡ በኢየሱስ በመዳናችን ምክንያት፡ እልል እያልን፡ እየተደሰትን ባየን ጊዜ፡ ያኔ በዚያን ጊዜ በጉ አለመታረዱን እንዴት እናውቃለን?

2 ዛሬ ምሽትም፡ በዳግም ምጽአቱ የሚገለጠው የመለኮታዊው ክብር ቀብድ፡ ቀምሰናል። ህመም እና ሐዘን በሙሉ የሚወገድበት ጊዜ ይመጣል። ያኔ እርሱን ፊት ለፊት እናየዋለንና፡ የክብር አካሉን የሚመስል አካል እንለብሳለን። አሁን እጆቻችን ሲሸበሸቡ፡ ጸጉራችንም ሲሸብት፡ ትከሻችንም ሲጎብጥ ስናየው፡ ሟቾች መሆናችንን እና ጭንቅላታችን ወዳጎነበሰለት፡ ወደ መጣንበት የምድር አፈር ጉዞ እያደረግን መሆናችን እናውቃለን። አንተ ግን፡ ጌታ አምላክ ሆይ፡ አምላክነትህ እርግጥ እንደሆነ ሁሉ፡ በዘመን ፍጻሜ ዳግም እንደምንነሳ ቃል ገብተህልናል፡ እኛም አምነናል።

3 ኢየሱስ እንድናደርገው ስላዘዘን፡ ዛሬ ማታ በፊትህ ከእምነት ጋር ለመቆም በድፍረት መጣን። ያደረግነው መልካም ነገር የለምና፡ በመልካም ስራችን አይደለም፤ ነገር ግን በሰጠን ጸጋ ምክንያት፡ ባለ ጸግነት ሁሉ የእኛ መሆኑን እያወጅን በታላቅ ትህትና እንቀርባለን። ስለዚህም፡ ቃል በሚገለጥበት ጊዜ በዚህ ምሽት ትባርከን ዘንድ እንማጸናለን። ደግሞም፦ "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡" ተብሎ ተጽፏልና። የእግዚአብሔርም አፍ ዛሬ ማታ ይናገረን። ቃሎቹ ይገለጡ፡ ወደ እኛም ወደ አድማጮች ልብ ውስጥ ይግቡ፣ በመንፈስህና በመገኘትህ ሙላን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለንና። አሜን።

4 ዛሬ—እና ትናንት፡ ማለት፡ ትናንት ማታ፡ እና ዛሬ፡ ስንነጋገርበት በቆየን ርዕሰ ጉዳይ፦ በመጀመርያ፡ ያነሳነው፡ **የሐይማኖት ተቋም ያልሆነው ለምንድነው** በሚል ነበር። እንደውም ጠንከር አድርገን፡ የሐይማኖት ተቋም ያልሆነው ለምንድነውን፡ በሐይማኖት ተቋማት ለምን እናምንም ብለነዋል። ምክንያቱ፡ ሐይማኖታዊ ተቋማት ከዲያብሎስ እንጂ፡ ከእግዚአብሄር ዘንድ የተሰጡ አለመሆናቸውን ከቅዱስ መጽሐፍ ስለተረዳን፤ ከመጽሐፍ ቅዱስም አረጋግጠናል። እና ያ፡ በሐይማኖት ተቋሞች በኩል፡ ብዙ ስህተት ያመጣል። አሁን ይህንን የምንለው ቤተ ክርስትያንን ለማረም እና ወደ ተባረከው የእግዚአብሔር ቃል ህብረት ለማምጣት ነው። ይህም ተሰፋችን፡ የሐይማኖት ተቋማት በሚሉት፡ ወይም ሰዎች በሚናገሩት ሳይሆን፤ እግዚአብሔር አምላክ በተናገረው ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው። በትክክል የምንቃናበት ብቸኛው መንገድም ይህ ነው።

5 ዛሬ ጠዋት፡ ከተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት የተውጣጡ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በፍፁም የሌሉ፡ በአርጕቷ እናታቸው፡ በጋለሞታዋ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚነገሩ፡ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚስግዱላቸው ሰብከቶች፡ እንደ ትምህርትም የሚያስተምሩት፡ ይመስለኛል አምስት፡ የተለያዩ ነጥቦችን ይዤአለሁ፡ እነዚህ ወደ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ገብቷል። እኛም የእግዚአብሔር ቃል ለሚቃረኑ ተመሳሳይ ነገሮች ሰገድን።

6 የመጀመሪያዋ የሐይማኖት ተቋም፡ ዛሬ ከሰአት በኋላ በኒቂያ አባቶች ታሪክ፣ በኒቂያ ቤተ ክርስቲያን አይተናታል። ሐዋርያት ከሞቱ በኋላ፡ የኒቂያ አባቶች የምንላቸው መጡ፡ እነኚህም እጅግ ብዙ አመታት ተጓዙ። ከሦስት መቶ ሃያ-አምስት ዓመታት በኋላ፡ በስተመጨረሻ—ወደ ኒቂያ፡ ታላቁ—የኒቂያ ጉባኤ፡ ወደተካሄደበት፡ ፈረንሳይ ተሰበሰቡ። እዚያም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አሁን ያላትን፡ እና ለፕሮቴስታንቶችም የተላለፈውን እነዚህን ዶግማዎች አቋቋሙ።

7 ዛሬ ጠዋት በ—ትምህርት ውስጥ እንዳልኩትም፡ "እስከ አሥራ አምስት መቶ ዓመታት፡ የጨለማ ዘመን—እስከ ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ድረስ፡ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ 'አሁንም ስሜ አለህ፡' ብሎ ያልተናገረው ዘመን አልነበረም።"

8 ከዚያ በኋላ ግን፡ በሐይማኖት ተቋም ሰሞች እንጂ፡ በክርስቶስ ሰም አልመጡም፡ "ካቶሊክ፣ ሉተር፣ ዌስሊ፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ጴንጤቆስጤ፣" ወዘተ።

9 ከዘመኑ መዝጊያ በፊት ግን፦ "እነሆ በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ፡" ይለዋል። አያችሁ? ያለንበት ዘመንም በማብቂያዋ የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን መካከል፡ በሚገኘው የተከፈተ-በር ዘመን፡ እየኖርን እንዳለን እናምናለን።

10 እስከ ሎዶቅያ ጉባኤ ድረስ ሶስት መቶ ሀያ-አምስት አመታት ናቸው። በእነዚያም መረጨት፣ ውኃን ማፍሰስ፣ እና የውሸት ጥምቀቶች፣ ሐሰተኛ መንፈስ ቅዱስ፣ የመሳሰሉ ነገሮችን አስተዋውቀዋል። ተቀብለውታልም።

11 ሉተርም፡ ካህን ሆኖ፡ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በወጣ ጊዜ፡ እነዚህን ይዞ ወጣ። ከሱ ዝዊንግሊ ወጣ፣ ከዝዊንሊ ካልቪን፣ ከካልቪን ዌስሊ ወጣ፣ ኦህ፡ ወዘተረፈ። እነዚያንም ዶግማዎችን ማስፈልፈል ቀጠሉበት። እርሱ እንዲጓዙበት ያላዘዛቸው መንገዶች እየተከተሉ፡ እግዚአብሔር እንዴት ቤተ ክርስቲያኑን ሊመራ ይችላል?

12 ደግሞም አስታውሱ፡ በራእይ 17፡ "ያቺን ሴት፡" እናገኛለን። አሁን እነዚህ ቃላት ግልጽ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፈዋል፡ መናገር እችላለሁ ብዬ አሰባለሁ። ሴቲቱንም "ጋለሞታ" ይላታል። ይህ ማለት ሴቲቱ መጥፎ-ሰም ያላት ሴት ናት፡ ባል አግብታ ትዳር ያላት ሰትሆን፡ ከዓለም ጋር አመንዝራለች። በዚህም **"የጋለሞታዎች እናት፡"** ተብላለች... ስለዚህ ሴቶች ልጆች ነበሯት። ከተቀመጠችበት መልክአ ምድራዊ አቀማመጧ ተነስተን... በተጨማሪም፡ እኔ ራሴ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ ትምህርቷንና ነገረ ስራዋ አይቻለሁ። ጌታም ከካቶሊክ ቤተክርትያን በቀር ሌላ ልትሆን እንደማትችል አድርጎ መሰመር እንዳሰመረባት አምናለሁ። ሊሆን የሚችለው ይህ ብቻ ነው። እሷስ እነማንን ወለደች? የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትን። በትክክል፡ ወልዳቸዋለች።

13 በእጇም የዝሙትዋን የወይን ጽዋ ነበራት፡ ለምድርም ነገሥታት ሁሉ ትሰጥ ነበር። እርሷም በመንፈሳዊ አነጋገር በምድር ሁሉ ላይ ገዥ ሆነች። ይህ በትክክል እውነት ነው። ሌላ አይደለም...

14 ተመልከቱ፡ አሁን፡ ወደ ዳንኤል እንመለስና ምስሉን ማየት እንችላለን። ምስሉን እዩት፡ የወርቅ ራስ፡ የባቢሎን መንግስት ነው፣ ነሐስ... ወይም ብር፣ ሜዶ-ና-ፔርሺያ፣ ነሓስ፣ የግሪክ መንግስት፡ አሌክሳንደር ዘ ግሬት፣ ወዘተረፈ፤ ከዚያም ሁለቱ እግሮች፡ ምስራቃዊ እና ምዕራባዊ ሮም፡ የሮማ ግዛቶች ናቸው።

15 ዛሬ በማለዳ እንደተናገርነው፡ ከአሥሩ ቀንዶች ጋር የሚመጡትን እነዚህ አሥር መንግሥታት ላይ አስተውሉ። ሊነሱ በተዘጋጁት አሥሩ መንግሥታት ሁሉ ላይ፡ የተደባለቀ ብረትና ሸክላ አለው። ብረቱም ከእግሮቹ ይወጣል፡ ይህም ሮም ነበር። ከሰማይ በታች ባለው በእያንዳንዱ ህዝብ ላይ፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በኩል የሮማኒዝም ቅይጥ አለበት። ይህ በትክክል እውነት ነው። እነዚህ ግን፡ መቼም መቀላቀል አይችሉም።

16 እርስ በርሳቸው ግን፡ ይጋባሉ። መጽሐፍ ቅዱስም ተናግሯል። ዛሬም ተመልከቷቸው። ወንድ ልጆችሁ ከካቶሊክ ሴት ወደ፡ ለመጋባት ሲሄዱ፡ ልጆቻቸውን ካቶሊክ አርገው ለማሳደግ ቃል ይገባሉ፣ አያችሁ፡ ወይም በተቃራኒው። አያችሁ፡ የአንደኛውን ስልጣን ለመሰበር ነው።

17 ይህ ሁሉ ግን ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስ ግልሙትና ይለዋል። አሁንስ ምን ታደርጉት ይሆን? አዎን። የህዝቡስ ሐጥያት መጨረሻው ምን ይሆን... ወደ ኋላ ተመልሰን በዘዳግም ካየን፡ ከህግ ውጭ የተወለደ ልጅ፣ ወይም ዲቃላ ልጅ፣ እስከ አሥራ አራት ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ መግባት እንደማይችል እናያለን። ያ እንደ ሕግ መሰረት ነው። ክርስቶስ ደግሞ ሕጉን ለማጠናከር መጥተዋልና። አሁን ምን ያህል ጠንክሮ ይሆን?

18 እነኚህስ ምን ይሆናሉ፡ ዛሬ በየጎዳናው የሚታዩት ቅምጥሎች እጣ ፈንታ ከየት ነው፡ ትንባሆ-ጠጪ፡ አጭር-ቀሚስ ለባሽ ሴቶች፡ ጸጉራቸውን-የሚቆራርጡ ቅምጥል ሴቶች፡ ወዘተ ከምን ተነስተው ነው? በምን ምክንያት ነው? ምክንያቱ'ማ የእናቶቻቸው ስራ እንዲሁ ስለነበረ ነው። ከአንዱ ትውልድ፡ ወደ ቀጣይ ትውልድ የሚተላለፍ፡ እርኩሰት ነው። ያ ነው። ታዲያ ምን አተረፍን? አንድ ነገር ላይ ደርሰናል፡ ይህም የቦካ የሐጥያት ክምችት ላይ።

19 እግዚአብሔር፡ ሩሲያን ያነሳሳበት ምክንያት፡ እንደ አንቲደሉቪያን ጎርፍ ደመናትን ጠርቶ፡ ምድር እንዳጠፋት ሁሉ፡ በአቶሚክ ቦምብ ትጠራርግለት ዘንድ ነው። አዎን፡ አነሳስቷታል። መጽሐፍ ቅዱስም ይናገራል። ሩሲያ፡ አምላክ አልባ የሆነች አገር፡ አምላክ አልባዋ፡ ሁሉን በሚችል አምላክ እጅ ስራዋን እየሰራች ትገኛለች። እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር መጓዝ ባለመቻላቸው ምክንያት በንጉሱ ናቡከደነፆር እንዳጠፋቸው ሁሉ፡ ካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ስላፈሰሰችው የቅዱሳን ደም "ስለ ቅዱሳን በቀል፡" ሩሲያ፡ አሁን እየተነሳች ትገኛለች። ሁሉንም ነገር ያሰወግዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል።

20 ስለዚህ ተመልከቱ፡ እናታቸው የዘፋኝ አጃቢ ከነበረች፡ እናቷም፡ አያታቸው ቅምጥል ከነበረች፣ ዛሬ እሷ ምን ትሆናለች? የሮክ-ኤንድ-ሮል ተወዛዋዥ ትሆናለች። ልጆቿስ ምን ይሆኑ ይህን?

እናንተም፦ “ይሄን ያደረገው እግዚአብሔር ነውን” ብላችኋል? የሰ፡ ሰር።

21 እግዚአብሔር የልጆችን፡ የትውልዱን ኃጢአት፡ እስከ አሥራ አራት ትውልድ ድረስ ይጐበኛል። እንግዲህ ክርስቶስ ሕጉን ሊያጎላ መጣ ካልን፡ “አንድ መቶ ትውልድ ወይም አምስት-መቶ ትውልድ፡” ማለታችን ነው። ለምን፡ እሱ ሲናገር፦ “ቀደምቶቹ፡ ‘አትግደል’ ብለው ሲናገሩ፡ ከቀደምቶቹ፡ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፡ ‘በወንድሙ ላይ፡ ያለ ምክንያት፡ የሚናደድበት፡ ነፍሰ ገዳይ ነው።’ የቀደሙት፡ ‘አታመንዝር፡’ ሲሉ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ ሴት አይቶ የተመኛት፡ ያን ጊዜ አመንዝሯል።” እንዲህ አርጎታል... **ማጠናከር** ምን ማለት ነው? “ብዙ ጊዜ ብዙ ማሳደግ ማለት ነው።” በሕጉ ሰር አሥራ አራት ትውልድ ከነበረ፡ ዛሬ ያንኑ ነገር እስከ ምን ይደርስ ይሆን?

22 ወጣት ወንዶች፡ እና ጎልማሳ-ወንዶች፡ ያገቡ ሰዎች ሁሉ የጋብቻ ቃላቸውን ማክበር ትተዋል። ምነው፡ ልክ እንደ ተራ ውሾች፡ አንዷን ሴት ጎትተው የትም ይኖራሉ። ከአንዳንድ ሰዎች ይልቅ ውሻ የተሻለ ክብር እና ሞራል አላት። ከባድ ንግግር እንደሆነ አውቃለሁ፡ ይሁን እንጂ እውነት ነው።

23 ለምን? አብያተ ክርስቲያናትም ጎን ለጎን ይጓዛሉ እንጂ ስለ ጉዳዩ ምንም አይናገሩም። ለምን? አብያተ ክርስትያንትም ሁሉ ወረሱት። የእናታቸው ስራ እየደገሙት ነው። ምክንያቱ፡ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የወጣ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች፤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኃጢአት በፕሮቴስታንቶች ላይ ይዘንባል። አዎን፡ ጀበና፡ እንሥራን “ቆሻሻ ነሽ” አትላትምና። በትክክል እውነት ነው።

24 አሁን አንድ ነገር አውቀናል፡ ቅዱስ ቃል ውስጥ፡ አንድ ነገር አውቀናል... ዛሬ እዚህ ጠረጴዛ ላይ አንድ ጽሑፍ አይታየኛም። እላችኋለሁ፦ “እግዚአብሔር የሐይማኖት ተቋም የሾመበትን አንድ ቦታ አሳዩኝ። እግዚአብሔር ሴትን ሰባኪ አድርጎ የሾመበትን አንድ ቦታ አሳዩኝ። እግዚአብሔር ውኃ መረጨት የሾመበት አንድ ቦታ አሳዩኝ። እግዚአብሔር ውኃን ማፍሰስ የሾመበት አንድ ቦታ አሳዩኝ። እግዚአብሔር ‘በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ።’ ስም አንድ ሰው ያጠመቀበት ቦታ አሳዩኝ እነዚህን ፈልጓቸው።” እኛ ግን ሳናቋርጥ እንደጋግማቸዋለን። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ናቸው።

25 አሁንም፡ እላችኋለሁ፦ “ባፕቲስት ያልሆንነው፡ ምክንያቱ፡ ምንድነው፡ ምክንያቱ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠመቁ እናምናለን። መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በዚህ ጥምቀት በቀር፡ በሌላ የተጠመቀ አንድም ሰው የለም። ‘በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ’ ተብሎ አንድ ሰው የተጠመቀበት ቦታ ካለ አሳዩን፤ ካሳያችሁኝ እጆቼን እንሰቼ ሐሰተኛ ነቢይ ነኝ እላለሁ።”

26 መጽሐፍ ቅዱስ ‘በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ’ ብሎ ካዘዘ፡ ይህ ማለት በዚህ መንገድ አድርጉት ነው። የቱንም ያህል ተጠምቀው የነበሩ ቢሆኑም፡ እንደገና መጠመቅ ነበረባቸውና። ጳውሎስ እንደገና እንዲጠመቁ አዘዛቸው። ኢየሱስ ክርስቶስን ባጠመቀ ሰው፡ በመጥምቁ በዮሐንስ ተጠምቀው ነበር። ጳውሎስ ግን ‘ያ ከአሁን በኋላ አያገለግልም። ኑና፡ እንደገና ተጠመቁ’ አላቸው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ከመቀበላቸው በፊት መታዘዝ ነበረባቸው። የእግዚአብሔር ፕሮግራም ነበር።”

27 ዛሬ ማታ፡ ከዚህ በበለጠ ጠልቆ መግባት እችላለሁ። ለምን? ኢየሱስ ቃሉን ይጠብቃልና። ታምናላችሁ? ዛሬ ጠዋት፡ ሁላችሁ በሚባል ደረጃ እዚህ የነበራችሁ ብትሆኑም፡ ትንሽ ተጨማሪ ነገር ማስቀመጥ እፈልጋለሁ።

28 ጳውሎስ ግን... ሰዎቹ ከተጠመቁ በኋላ ያንን ትዕዛዝ መስጠቱ ለምን አስፈለገው? ጳውሎስ፦ "የሰማይ መልአክም ይሁን፡ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን" ብሏል።

29 እናንተም "አዲስ ብርሃን አግኝተንበታል፡" ትላላችሁ። በፍጹም፡ አታገኙም። ዲያብሎስ ወደ ሔዋን የመጣው፡ እንዲህ አይነቱ አዲስ ብርሃን ይዞ ነው። እግዚአብሔር አስቀድሞ በሰጠው ብርሃን ውስጥ መሄድ አለባችሁ እንጂ። አዲስ ብርሃን አያስፈልጋችሁም፡ ያ ነው።

30 አሁን ምን ያህል ቀላል እንደሆነ፡ ተመልከቱት። ከደብረ ታቦር ተራራ በወረዱ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፦ "ሰዎች እኔን የሰው ልጅን ማን ነው ይሉኛል? "

"አንዳንዶች 'ሙሴ፣ ወይም ኤልያስ፣ ወይም ከነብያት አንዱ ነው ይላሉ።'"

"እናንተስ ማን ነው ትሉኛላችሁ? " አላቸው፤

31 ጴጥሮስም፦ "አንተ ክርስቶስ፡ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፡" አለው።

32 እርሱም "የዮና ልጅ፡ ስምዖን ሆይ፡ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና፡ ብፁዕ ነህ፡" አለው። አያችሁ፡ በትምህርት አይመጣም። ከሐይማኖት ተቋም አይመጣም። "ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም። ከሰነ መለኮት ትምህርት ቤት በፍጹም አልተማርከውም። በሰማያት ያለው፡ አባቴ ግን፡ ይህን ገልጦልሃል። በዚችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም፡" እሱ ማን እንደሆነ በሚታወቅበት በመንፈሳዊ መገለጥ ላይ።

33 አስተውሉ፦ "እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ። የመንግስተ ሰማያት መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ። በምድርም ላይ የምታስረውን ሁሉ፡ በሰማይ እኔ አስረዋለሁ፡ በምድር ላይ የምትፈታውን ሁሉ እኔ በሰማይ እፈታዋለሁ።" እንግዲህ፡ እግዚአብሄር ቃሉን ይጠብቃል ካልጠበቀ ግን አምላክ አይደለም። እንግዲህ፡ ያንን ባደረገ ጊዜ፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ፡ ተሰቀለ፣ ተነሣ፣ ወደ ሰማይም አረገ፣ ጴጥሮስም በበዓለ ሃምሳ ቀን ወንጌልን ከፈተው። ከፍቷል አልከፈተም? እዎን፡ በርግጥ፡ ከፍቷል። አሁን ተከታተሉ፡ በከፈተው ጊዜ...

34 መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ላይ ወርዶ ተሞልተው ስለነበር፡ ሌሎች አፌዙባቸው። "መናፍቃን፡ ሆሊ-ሮለሮች፡" ወይም በመሳሰሉ አይነት ሰሞች ይጠሯቸው ጀመር። እየተሳለቁም፡ "ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል፡" አሉአቸው።

35 ጴጥሮስ ግን በመካከላቸው ቆሞ፡ ድምጹን ከፍ አድርጎ፡ እንዲህ አለ፦ "ወንድሞቼ ሆይ ሁላችሁም ሰዎች ሆይ፡ ድምፄን ስሙ። ቃሌንም አድምጡ ስሙኝም። ከቀኑ ሦስት ሰዓት ነውና፡ እናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ ሰዎች የሰከሩ አይደሉም። ነገር ግን ይህ በነቢዩ ኢዩኤል እንደተነገረ፦ 'እንዲህም ይሆናል በመጨረሻ ዘመን፡ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፡' በዚያ ቀን፡ በወንድ እና

በሴት ልጆቹ፡ በፈጠራቸው፡ እና በሌሎች ሁሉ፡ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ዘረዘረ።"

36 ይህን መስማት በጀመሩ ጊዜ፡ ልባቸው ተነካ። ምክንያቱ፡ ሀሁ´ን ያልቆጠረ ሰው ይሄን ሲናገር ሰምተው፡ በውስጡ የሚቀጣጠል ቁምነገር፡ መንፈስ ቅዱስን አይተው፡ የሆነ ነገር እንዳለው አስተውለዋል። እሱን ማስቆም? ኧረ፡ ብርቱ ነፋስ በሚነፍስበት ቀን፡ ከደረቅ ህንጻ፡ እሳትን ማጥፋት መሞከር ነው። አትችሉም። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል። ከዚያስ ምን አደረገ?

37 ሰዎቹም፡ "እናንተ ሰዎች፡ እናንተ ወንድሞች ሆይ፡ እኔድን ዘንድ ምን እናድርግ" ብለው ጠየቁ?

38 አሁን አስተውሉ፡ ጴጥሮስ ሆይ፡ የመንግስት መክፈቻዎች በእጅህ ናቸው። አያችሁ?

39 ኢየሱስ፡ በሦስተኛው ቀን በተነሳ ጊዜ፡ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻዎች አልያዘም ነበር። ይህን ታውቃላችሁ? "የሞት እና የገሃነም መክፈቻዎች አሉኝ፡" ብሏል፡ የመንግስተ ሰማያት መክፈቻዎች ግን ለጴጥሮስ ስለ ሰጠው አለኝ አላለም።

40 እርሱም፦ "ጴጥሮስ ሆይ፡ በምድር የምትፈታው፡ በሰማይ እፈታዋለሁ። በምድር የምታስረውም፡ እኔ በሰማይ አስረዋለሁ" ብሎት ነበር።

41 ስለዚህ ይህ በረከት ለዓለም ሁሉ ይከፍት ዘንድ፡ መክፈቻዎችን ይዞ ቆመ። እነሆ መክፈቻዎችን በእጁ ይዟል። ሰዎቹም፡ "እንድን ዘንድ ምን እናድርግ" ብለው ይጠይቁታል? እንግዲህ፡ እግዚአብሔር ስልጣን ከተሰጠው፡ ሐዋርያው ይደረግ ለሚለው ነገር ሁሉ፡ በሰማይ እውቅና መስጠት የራሱ ግዴታ ነው።

42 ጴጥሮስም "ንስሐ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ስለ ኃጢአቶቻችሁም ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" ልክ ነው? መክፈቻዎቹ ለሌላ ስም፡ በሌላ መንገድ፡ ወይም—ለሌላ ዓይነት ቅርጽ በሰማይ ላይ እሺ የማይሉት ለዚህ ነው። በምድር አይሰራም፣ በሰማያትም አይሰራም፣ ካልሆነ ግን ኢየሱስ ለጴጥሮስ የገባውን ቃል አልጠበቀም። ከዛ በኋላ የተጠመቁ ሰዎች ሁሉ፡ መጽሀፍ ቅድስ ውስጥ የተጠመቁት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። ከዚያ በፊት ተጠምቀው የነበሩ ሳይቀሩ፡ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት፡ መጥተው እንደገና በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ መጠመቅ ነበረባቸው። ትክክለኛው ያ ነው። አሁንም በተመሳሳይ መልኩ ይሰራል።

43 ስለዚህ፡ ጥምቀትን "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣" ስም ነው ብለን እያስተማርን ከሆንን የውሸት ትንቢት ነው። አሁን እንናተን መጉዳት አልፈልግም፡ ነገር ግን ይህች ቤተ ክርስቲያን ምን እንደሆነ እንድታውቅ ይህን መዘርዘር አለብኝ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ የቆምንበት ስፍራ የምናውቅ ሰዎች ስለሆንን መጣን እንጂ፡ ቂሎች እና መሃይሞች ስለሆንን አይደለም። በዚህ ስፍራ ላይ "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ" ስም የተጠመቀ ሰው አለ ብሎ ሊያሳየኝ የሚችል አንድ ሰው ካለ ይምጣ። አሁንስ የሐሰትን ትንቢት ወይስ እውነትን መስማት ትፈልጋላችሁ? ቃሉን መርምሩት። ሐላፊነታችሁ ነውና።

44 መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ—አንዲት ቤተ ክርስትያን የሐይማኖት ተቋም ሆና የተሾመችበት ሰፍራ፡ የሚያሳየኝ ካለ ይምጣ። ሴት ሰባኪ የሾመበትን ቦታ በመጽሐፍ ቅዱስ አሳዩኝ። እየተናገርን ያለነው እነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሾሙበትን ሰፍራ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳዩኝ። ምንም የለም። አንድ ሰፍራ አሳዩኝ። ወደ ሐይማኖት ተቋም ስትሄዱ...

45 ሜቶዲስቶች በተነሱ ጊዜ፡ አዎን፡ ቅድስናን ሰብከዋል። ይህም መልካም ነው። ከዛ በኋላ ግን፡ የሐይማኖት ተቋም መሰረቱ፡ መጨረሻቸውም ያ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ "ስም አለህ፡" የሚልበት ምክንያትም ይህ ነው።

"ክርስቲያን ነኝ፡" ትላላችሁ።

"ወድያው፡ ከየትኛው ተቋም ነህ? "

46 እናንተም፡- "ከሜቶዲስት" ትላላችሁ፤ እንግዲያውስ፡ አመንዝራ ናችሁ። "ባፕቲስት ነኝ፡" አመንዝራ ናችሁ። "ጴንጤቆስጤ፣" አመንዝራ ናችሁ። የቤተ ክርትያኒቱ ናችሁ።

47 የክርስቶስ መሆን አለባችሁ። "ሜቶዲስት፣" "ባፕቲስት፣" ነኝ አትበሉ። ክርስትያን ከሆናችሁ፡ ከልብ ክርስትያን ናችሁ።

48 እውነት ነው፡ እነዚህ የሐይምኖት ተቋማት እያንዳንዳቸው ልጆችን፣ የእግዚአብሔርን ልጆችን ማፍራት ይችላሉ። ነገር ግን ሜቶዲስት ወይም ባፕቲስት ስለሆንክ ብቻ፡ ወደ መንግሥተ ሰማይ እገባለሁ ብለህ ካሰብክ ተሳስተሃል። እኛም ከዚህ አይነት ነገር የራቅንበት ምክንያት ይህ ነው።

ባፕቲስቶች ለምን ማየት ተሳናቸው?

49 ከረጅም ጊዜ በፊት፡ የመመረቂያ ጽሑፉን የሚያዘጋጅ አንድ ሜቶዲስት፡ ጥያቄ ጠየቅኩት። እርሱም "እኛ አንተን የምንቃወምበት ብቸኛ ነገር፡ ጴንጤቆስጤዎች ጋር መሆን ስለምታበዛ ነው፡" አለኝ።

"'እኛ' ማለትህ እነማን ናችሁ? " አልኩት፤

"እኛ፣ ሜቶዲስቶች።"

50 እኔም "እሺ፡ ምን እንደማደርግ ልንገርህ። ወደ ከተማችሁ ልምጣና ሜቶዲስቶች ስፖንሰር እንዲያደርጉ አድርግ፡" አልኩት።

"አይ፡" "አይሆንም፡ ይሄን'ማ ማድረግ አንችልም፡" አለ።

51 እኔም፡- "የገመትኩትም ይህ ነው። ከጴንጤቆስጤዎች ጋር የምሆንበት ምክንያት እነሱ ስለሚያምኑት ነው። ትክክል። በዙርያው ይሰፍራሉ። የሚጠቀሙበትም እነሱ ናቸው።"

52 ስለ ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፡ በቅርብ ጊዜ፣ **በላይፍ** መጽሔት የወጣ ጽሑፍ ያነበባችሁ ሰንቶች ናችሁ? በዚህ ዘመን ካሉት ታላላቅ ክስተቶች አንዱ ነው። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተደምረው በአንድ ዓመት ውስጥ ካሳመኗቸው ሰዎች ይልቅ ብዙ አማኞችን ቀይሯል ይላል። ለምን? እውነትን ስለ አመኑ ደግሞም ስለሚኖሩት፡ እስከነ ጥፋታቸውም እንኳ፡ እግዚአብሔር በመካከላቸው ይሰራል። እውነት ነው።

53 አሁንስ ምን እየሰራን ነው? አያችሁ? የሐይማኖት ተቋም የማንሆንበት ምክንያት ይህ ነው። በእርግጠኝነት ግን ጴንጤቆስጤ ተቋም ሆኗል...

54 ያኔ ድሮ፡ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት፡ መንፈስ ቅዱስ በጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስትያን ላይ በወረደ ጊዜ፡ ከስጦታዎች አንዱ የሆነውን፡ ልሳን መናገር ጀመሩ። ያውም ከስጦታዎቹ ሁሉ ትንሹ ስጦታ እሱ ነው። እንደ ቅዱስ ጳውሎስ መሰረት፡ ከሁሉ ይልቅ ያነሰ ስጦታ፡ በልሳን መናገር ነው። ልክ በወረደ ጊዜ፡ "ኦህ፡" "አሁን አገኘነው፡" አሉ፡ በዚሁም አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ የተባለውን፡ ጠቅላይ ምክር ቤት፡ የሐይማኖት ተቋም አድርገው መሰረቱ። "ኦህ፡ ልሳን ያልተናገረ ሰው አልተሞላም አሉ፡" እግዚአብሄር ግን በደረሱበት ቁጭ አርጓቸው ተንቀሳቀሰ። በትክክል። የሰ፡ ሰር።

55 ከነርሱም ዋንነሶች ተነሱ፡ ጥምቀት በኢየሱስ ስም ነው የሚል እውቀት ላይ ደረሱ። "ኦህ፡ አገኘነው" አሉ፡ በዚያም ተደራጁ። ምንስ ያደርጋሉ? እግዚአብሔር ግን በደረሱበት ትቷቸው ወደፊት ቀጠለ።

ለማን፦ "የተጠማ ሁሉ፡ ይምጣ።"

56 አያችሁ፡ ዋንነስ፡ ወደ አሰምብሊዎች አይሄዱም። አሰምብሊዎችም ወደ ዋንነስ አይሄዱም። አሉ የተባሉ ምርጥ ሰዎቻቸው፣ ሚስተር ጎዝ እና ዶክተር ፖፕ እና ሌሎችም አነጋግሬያለሁ። ሰዎቹ ታላላቅ ሰዎች ናቸው... አብሬአቸው ቁጭ አልኩኝ። "የተማራችሁ ሰትሆኑ፡ ልሳንን እንደ ቀዳሚ ማረጋገጫ አድርጋችሁ እንዴት ታስተምራላችሁ፡" ብዬ ጠየቅኳቸው?

57 "እንደው፡" "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡" አለኝ፡ ከመካከላቸው፡ አንድ ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች፡ በቅንነት፡ እንዲህ አሉኝ፦ "ስሕተት እንደሆነ እናውቃለን፡ ነገር ግን ምን ልናደርግ እንችላለን? በአሁኑ ሰዓት አንዳች ትንፍሽ ብንል፡ አየህ፡ መላ ፕሮግራሙን ይሰናከላል።" ትክክል፡ እናንተም ቢሾፖች አትሆኑም፣ የበላይ ጠባቂ የመሆን ህልማችሁ ይቀራል። ችግራችሁ ይህ ነው።

58 ወንድሜ፡ እውነት፡ የምናገረው ነገር እውነት እንደሆነ እውቄ፡ ጥድ ዛፍ ስር ሆኜ እየሰበኩ፡ እውነት ይዤ፡ ጥግ ላይ ትንሽ አገልግሎት ብትኖረኝ እመርጣለሁ። ሰው እውነትን ይፈልጋል። እናንተም እንደ ክርስቲያን፡ እውነተኛ ምስክርነት የማስተላለፍ፡ ግዴታ አለባችሁ። በእግዚአብሔር ዘንድ ያስጠይቃችኋል።

59 እንግዲህ፡ ስለ እነኚህ ነገሮች፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተጠመቃችሁ ካልሆናችሁ፣ እነዚህን አልፈጸማችሁም፡ መንፈስ ቅዱስንም አልተቀበላችሁም...

60 "ምነው፡ እኔ'ኮ በልሳን እናገራለሁ፡" ትላላችሁ። ያ መንፈስ ቅዱስን ተሞልታችኋል ማለት አይደለም።

61 ጠንቋዮች፣ መተተኞች፣ አጋንንቶች፣ እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ በልሳኖች ሲናገሩ አይቻለሁ። በእውነት። መንፈስ ቅዱስ የላቸውም፡ እናንተም ታውቃላችሁ። ከሰው ቅል ደም እየጠጡ፡ እየጨፈሩ፡ በልሳኖችም እየተናገሩ፡ ሰይጣንን ይጠሩታል። በእውነት። መንፈስ ቅዱስ የላቸውም።

62 ስለዚህ፡ በልሳን ስለተናገርክ፡ አገኘኸው ማለት አይደለም። እንዳገኘኸው የምታውቅበት ብቸኛው መንገድ፣ መንፈስህ ከመንፈሱ ሲመሰክር፣ እና የመንፈስ ፍሬዎች፡ ፍቅር፣ እምነት፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ በጎነት፣ የውሃት፣

ጨዋነት ሲከተሉህ ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስን እንዳገኘህ የምታውቀው ያኔ ነው። እሱ ራሱ ስለራሱ ይመሠክራልና።

63 አሁን፡ አሰምብሊስ ወይም ባፕቲስት፡ ወይም ደግሞ ፕረስባይተርያን፡ ስለሆናችሁ ብቻ፡ ትክክል ነኝ ብላችሁ ካሰባችሁ፡ ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ አውቃችኋል? የአመንዝራ ሴት ሰም እየተቀበላችሁ ነው። ይህ በትክክል እውነት ነው። ከዚያ ነገር ውጡ። ከዚህ ራቁ። ከቤተ ክርስቲያናችሁ ውጭ ማለቴ አይደለም፤ እሱን የወደዳችሁት ታደርጉታላችሁ። እንደ'ኔ ግን "ኦህ፡ እኔ ፕረስባይተርያን ነኝ። እኛ በተአምራት ዘመን አናምንም፡" ከማለት ውድቀት ውጡ። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነውና። ለምን አታምኑትም? "ኦህ፣ እኔ ቸርች ኦፍ ክራይስት ነኝ። የተአምራት ዘመን አልፏል ተብሏል።" ሐሰተኛ ነቢያት ናቸው።

64 ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ድውያንን ለመፈወስ፣ ሙታንን ለማሥነሳት፣ አጋንንትን ለማስወጣት፣ ኃይልን የት እንደሰጣት አሳያችኋለሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጌታ ይህንን ሰልጣን ከቤተ ክርስትያን ወሰዶታል ብሎ ሊያሳየኝ የሚችል አንድ ሰው ካለ አሁን እወራረዳለሁ። የወሰደባችሁ ምንድነው? የገዛ ዶግማዎቻቹ፡ እንጂ፡ የጌታ ቃል አልወሰደባችሁም። መንፈስ ቅዱስ ግን፡ አሁንም እንደ ድሮው ሥራውን እየሰራ ነው፡ ለዘላለምም ይሰራል።

65 የሐይማኖት ተቋም ያልሆነበት ምክንያት ይህ ነው፡ "የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉንም ግን ክደዋል፡ ከእንዲህ ዓይነቱ ተለይ።" በእነዚህ ነገሮች አናምንም።

66 አሁን፡ የነገሩ አጀማመር እንዴት ነበረ? እንዴት እንደጀመረ ለማወቅ፡ በተቻለ ፍጥነት ወደዚህ ለመድረስ መቸኮል አለብን። ስለ መንፈስ ቅዱስ የተጻፉ ብዙ ቅዱሳት ቃላት አሉ።

67 ሌላ ደግሞ፡ ትላንት ማታ፡ "የቅዱሳን ጽናት፡" በሚል ጉዳይ ላይ ባፕቲስቶች እንደሚሉት፡ እንዳልሆነ ተወራርደን ነበርን። ኖ፡ ስር። ከባፕቲስቶች የካልቪኒዝም አመለካከት፣ እና ፅንሰ ሀሳብ ጋር በርግጥ እለያያለሁ። ከፕሬስባይቴሪያን ጋር በእርግጠኝነት አልሰማማም። በሜቶዲስቶች አርመናዊ አስተምህሮአቸው አልሰማማም። የስ፡ ስር። ይሁን እንጂ ሁለቱ እውነት አላቸው፡ እውነቱ የት እንደሆነ ለማወቅ ግን እናንተን **ወደዚህ** መመለስ አለብኝ። በዚያ መንገድ ስትጓዙ፡ እንደ እብድ ትሮጣላችሁ። በትክክል።

68 ባፕቲስቶች መጥተው፡ በጥልቅ ውሃ፡ ጥቂት ሰዎችን ያጠምቃሉ፡ ሰባኪው መጥቶ ያጠምቃቸዋል፡ ከአሥሩ ዘጠኙ ትንባሆ ያጨሳሉ፣ ወደ ኋላቸው ተመልሰው፡ ሌሊቱን በሙሉ፡ ካርታ እና ቡንኮ ሲጫወቱ ያድራሉ፡ ተሯሩጠው፡ ክፉ ንግድ ላይ ይደራደራሉ፤ ሴቶችም አጫጭር ልብሶች ለብሰው፣ ጸጉራቸውን ቆራርጠው፣ ትንባሆን—እያቦነኑ፡ ለወሬ፡ ለስቲች-እና-ለሶው ፓርቲዎች ስፈር ለስፈር እየዞሩ፡ ቆሻሻ ቀልዶች ያወራሉ። ይሄን ክርስትና ትሉታላችሁን? የዘላለም ደህነንት ያገኛችሁም ይመስላችኋልን? እንደዛው ወደ ሲኦል ትወርዳላችሁ። በምንም አይነት መልኩ በገነት አትደሰቱም። በፍጹም። ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ዳግም ሲወለድ ነው እንጂ።

ይሄኛው ዘለአለማዊ ደህንነት አይደልም...

69 እናንተ ጴንጤዎች ሆይ፡ ወደላይ-እና-ወደታች ስለዘለላችሁ፣ በልሳን ስለተናገራችሁ፣ ወለሉ ላይ ወደላይ-እና-ወደታች ስለሮጣችሁ፣ ዘላለማዊ ደህንነት አገኛችሁ ማለት አይደለም። በአእምሮአችሁ ውስጥ በጭራሽ አታስገቡ። ኖ፡ ስር። በፍጹም አይሆንም። ምክንያቱ፡ የገዛ—ህይወታችሁ፡ ምስክርነት፡ ፍሬአችሁ በጌታ ፊት ትክክል እንዳልሆነ ራሳችሁ ታውቁታላችሁ። ይህ ትክክል ነው። ሰታችኋል። ያ አሁንም ዘላለማዊ ደህንነት አይደለም።

70 አንድ ነገር ግን ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። የዘላለም ደህንነት አለን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለ ይመሰክራል። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሰማችን በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ እንደተጻፈ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል።

71 ዛሬ ጠዋት እንዳልኩት፣ እንደገና እላለሁ። “ዛሬ ማታ አንድ ሰም በእርያም ተጻፈ፡ እርሱም የኔ ነው፡” የሚል ዝማሬ የጻፈ ሰው፡ ሐሳቡ ትክክል ነበር፣ በመጽሀፍ ቅዱስ መሰረት ግን፡ ተሳስቷል። ሰማችሁ የተጻፈው በዳናችሁበት ምሽት አይደለም።

72 እንደ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እንደ ራዕይ 13፣ 17፣ እና የመሳሰሉት መሰረት፡ ሰማችሁ፦ “ዓለም ሳይፈጠር በፊት የተጻፈ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስም ዓለም ሳይፈጠር በፊት ታርዷል።”

73 እንዴት፡ ፍጻሜ የሌለው አምላክ ሲሆን፡ ፍጻሜ የሌለው አምላክ ሆኖ፡ መጨረሻውን ከመጀመሪያው የሚያውቅ ሆኖ፣ ለምክንያት ካልሆነ በቀር፡ በምድር ላይ ኃጢአት እንዲመጣ እንዴት ፈቀደ?

74 አሁን የተናገርናቸውን አንዳንድ ነገሮች ለማጠናከር ያህል። ከአዳኝ እና ከኃጢአተኛ፡ መጀመሪያ የነበረው ማን ነው? [አንድ ሰው “አዳኝ፡” አለ።—አርታዒ።] አዳኝ፡ በትክክል። ከአዳኙ እና ከኃጢአተኛው፡ ማን ይበረታል? አዳኝ ሐጥያትን ማስወገድ ከቻለ፡ እሱ ይበረታል። እሺ፡ በመጀመሪያ ኃጢአት እንዲገባ ለምን ፈቀደ? አዳኝ መሆኑን ለማሳየት። ከፈዋሹ እና ከበሽታው፡ ማን ይበረታል? ፈዋሽ ይበረታል። ታዲያ በሽታ እንዲገባ ለምን ፈቀደ? ፈዋሽ መሆኑን ለማሳየት ነዋ። አሁን መንፈሳዊነት ተሰማኝ። የሰ፡ ስር። ኦህ፡ ማይ! መገለጫዎቹ እነኚህ ናቸው።

75 ችግር እንዲመጣ የሚፈቅደው ለዚህ ነው። ደስታ መሆኑን ለማሳየት፡ ሀዘን እንዲመጣ ይፈቅዳል። አዎን፡ እንዲሁ ነው። ቀን መኖሩን ለማረጋገጥ፡ ሌሊት መሆኑ ግድ ነው። ሰላም መኖሩ ለማሳየት፡ ቁጡዎች እንሆናለን። አዎን፡ ጥቅም እና ጉዳት ነው። አቤት፡ እርሱ ድንቅ ነው።

76 እሺ፡ አጀማመሩ እንዴት ነበረ? ሌሊቱን በሙሉ እንዳላቆያችሁ፡ በተቻለን ፍጥነት፣ በቀጥታ እንገባበታለን። አሁን፡ የነገሮች ሁሉ መጀመሪያ መኖሩ ግድ ነው።

77 አንድ ነገር ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። ምናልባት ይሄኛው... በውስጥ ኪሳችሁ አስገቡ። እንጂ ከመደበኛው ምግብ ላይ መደመር አይገባችሁም። ግን አዳምጡት።

78 እናንተ ዘለአለማዊያን ፍጥረት ከሆናችሁ፡ መጀመርያም ይሁን፡ መጨረሻ የሌላችሁ ናችሁ ማለት ነው። **ዘላለማዊ** ማለት “መጀመሪያም መጨረሻም የሌለው፡” ከሚል ቃል የመጣ ነው።

79 ጠዋት ያልኩትን አታስታውሱም? ዛሬ ጠዋት፡ እንደተናገርኩት፡ አብርሃም ነገስታትን ገድሎ ሲመለስ፡ መልከ ጼዴቅ አገኘው። መጽሐፍ ቅዱስም በዕብራውያን ምዕራፍ 7 ላይ፦ ሌ—ሌ "ሌዊ በአባቱ በአብርሃም ወገብ ሳለ፡ ለመልከ ጼዴቅ አሥራትን ሰጠ፡" ይላል። አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፣ ይስሐቅ ያዕቆብን ወለደ፣ ያዕቆብ ሌዊን ወለደ። ያ ማለት አባት፣ አያት እና ቅድመ-አያት ነበሩ። ስለዚም መጽሀፍ ቅዱስ፡ ሌዊ በቅድመ-አያቱ ወገብ ውስጥ ሆኖ፡ ለመልከ ጼዴቅ አሥራት መክፈሉን ያረጋግጥለታል። ስለ ዘለአለማዊነት ከተናገርን! ማይ፡ ማይ! "በትክክል ከፈለ እንጂ፡ በምሳሌ ወይም በጥላ ከፈለ፡" በጭራሽ አይልም። መጽሐፍ ቅዱስ "አስራት ከፈለ፡" ይላል። አሜን።

80 ስለዚህ፡ ወደ ትክክለኛው ዘር ስንመጣ፡ ጳውሎስ ወንጌልን በሚሰብክበት ጊዜ እኔም በዚያ ነበርኩ እናንተም ነበራችሁ። በትንሽ ደቂቃዎች፡ ወደዚያ እንገባለን፡ ጀሮዎቻችንን እናስተካክል። አስተውሉ፡ ከጥንት ጀምሮ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እኛ የሚናገረው ይህ ነው።

81 እስቲ አስቡት! ሌዊ፤ ከዛ አባቱ፡ ያዕቆብ፣ ከዛ አባቱ፡ ይስሐቅ፤ ከዛ አብርሃም፡ አባቱ፤ ቅድመ-አያቱ። ሌዊ በቅድመ-አያቱ ወገብ በነበረ ጊዜ፡ ለመልከ ጼዴቅ አሥራትን ከፈለ።

82 እስኪ ልጠይቃችሁ። በኢዮብ 27… 38 ላይ፡ "የምድርን መሠረት ባደረግሁ ጊዜ የት ነበርክ፡ ብሎ የተናገረው፡ ይህ ማን ነው? የንጋት ከዋክብት አብረው ሲዘምሩ፡ የእግዚአብሔርም ልጆች በደስታ እልል ሲሉ? " በደስታ እልል ያሉ የእግዚአብሔር ልጆች እነማን ነበሩ? ኢየሱስም፡ እንዲህ አላቸው፦ "ዓለም ሳይፈጠር በፊት ከእናንተ ጋር ደስ ይለኛል።" የዘላለም ፍጥረት እንጂ። የጊዜ ፍጥረት አይደለንም።

83 "አባቴ ካልሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። ወደ እኔ የሚመጣውን ሁሉ፣ የዘላለም ህይወትን እሰጠዋለሁ፣ በመጨረሻው ቀንም አስነሳዋለሁ። ለእኔ ከሰጣቸው ከአባቴ እጅ፡ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም።" እንዴት ልትሸነፍ ትችላለህ?

84 አያችሁ፡ ፈርታችኋል። ትፈራላችሁ። ወዲያ ወዲህ ትሮጣላችሁ። በዓለም ላይ፡ ገና መሆናችሁ፡ ትክክለኛ ማረጋገጫው ይህ ነው። ትክክል ነው። እንዲህ ከሆነ እግዚአብሄር እንዴት ያድናችኋል…

85 እስኪ እግዚአብሄር ፍጻሜ የሌለው መሆኑን አምናችሁ፡ እጆቻችሁን ከፍ የምታደርጉ ስንቶች ናችሁ? **ፍጻሜ የሌለው** ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? በቃ ፍጹም ነው። ፍጻሜ የሌለው፡ ይህ **ፍጻሜ የሌለው** የሚለውን ቃል መተንተን—አትችሉም።

86 የካሜራችሁን ሴቲንግ ኢንፊኒት ላይ አድርጋችሁት ታውቃላችሁን? ይህ ማለት፡ ከወዲያ ማዶ ማለት ነው። መልካም። ቀጥሎ የአትኩሮት ወሰን አይኖረውን።

87 እግዚአብሔርም፡ እንዲህ ነው። ፍጻሜ የለውም። እሱ ፍጻሜ የሌለው ከሆነ፡ ጥንዚዛ ይሁን፣ ዝንብም ይሁን፣ ቁንጫም ይሁን፣ ቅማል፣ መዥገር፣ ወይም አሁን በምድር ያለ፡ ወይም ከአሁን በኋላ የሚመጣ የትኛውም ነገር፡

እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር በፊት ያውቀዋል። ስለ ፍጻሜ የሌለው አንዳንድ ጽንሰ ሐሳቦች አሉ።

88 እንግዲህ፡ ይህ፡ ፍጻሜ አልባው እግዚአብሔር፡ በሚቀጥለው ሳምንት፣ ወይም በቀጣይ ወር፡ እንደሚያጣህ እያወቀ አንተን ካዳነ፡ የገዛ ዓላማውን እየደፈረ ነው። ሊያጣህ አይችልም። “ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ ከቶ አይመጣም።” አያደርገውም። እናንተም እንዲሁ…

89 “ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን አያደርግም፡ የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ይኖራልና ኃጢአትንም አይሠራም።” የኃጢአት-መስዋዕት እያለለት እንዴት ኃጢአት ሊሠራ ይችላል?

90 ፍጹም ጤና ላይ ሆኜ እንዴት እታመማለሁ? ማየት እየቻልኩ እንዴት እታወራለሁ? ኡህ፡ ማይ! በተመሳሳይ ጊዜ በህንፃው ውስጥ እና ከህንፃው ውጭ እንዴት መሆን እችላለሁ? በተመሳሳይ ጊዜ ሰካራም እና ንቁ እንዴት እሆናለሁ? መሆን አትችሉም።

91 በዳናችሁ ጊዜ፡ ከሐጥያት ስርየት በታች ትሆናላችሁ፡ ኃጢያቶቻችሁም በእናንተ ላይ አይቆጠሩም። ዳዊት “እግዚአብሔር ኃጢአቱ የማይቆጥርበት፡ ኃጢአትቱ የተከደነለት ሰው ምስጉን ነው፡” አላለምን? እግዚአብሔር ኃጢአትን በፍጥረቱ ላይ አይዝም። ጠንከር ቢልም። የተጣራ ወተት ባይሆንም። ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። እግዚአብሔር በጻድቃን ላይ ኃጢአትን አይቆጥርም።

92 “እግዚአብሔር” በጸጋው፡ እና አስቀድሞ በመወሰን፣ “ሁሉም ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ፡ ማንም እንዲጠፋ አልፈለገም።” ነገር ግን ፍጻሜ የሌለው በመሆኑ፡ ማን ይመጣል ማን አይመጣም ያውቃል። ሁሉም ለፈቃዱ እንዲሰራ ሁሉንም አስቀድሞ መወሰን ይችላል። እንዲህ ካላደረገ ግን፡ ታዲያ ኃጢአት መፍቀድስ ለምን አስፈለገው? እሱ አዳኝ ለመሆን… ኃጢአተኛ ባይኖር ኖሮ፡ አዳኝ ባልሆነም ነበር፡ በእርሱ ውስጥ የነበረው፡ መገለጫ፡ ሊወጣ አይችልም ነበር።

93 እንዴት ፈዋሽ ሊሆን ቻለ? እንዴት ፈዋሽ ሊሆን ቻለ? ራሱን ፈዋሽ መሆኑን ያሳይ ዘንድ ህመም እንዲመጣ ስለ ፈቀደ። ፈዋሽ ነበርና። እንዴት ሊሆን ይችላል… እንዴትስ ሊታወቅ ይችል ነበር? መገለጫውስ በምን መልኩ ሊሰራ ይችል ነበር? መቼም በሽታ ባይኖር፡ እንዴት ፈዋሽ ሊሆን ይችላል? በሽታን መፍቀድ ነበረበት።

94 ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 8 ላይ “አንተ ሞኝ ሰው ሆይ፡ ሸክላ ሠሪውን—እንዲህ አድርግ ማን ይለዋል፤ ሸክላ ተነስታ፡ ‘አንተ፡ ለምን፡ እንዲህ ሰራኸኝ፡’ ትለዋለችን? ክብሩን በግብፅ ያሳይ ዘንድ፡ ፈርዖንን ያስነሣው ለዚሁ ዓላማ አይደለምን? የወደደውን ይምረዋል፡ የወደደውንም እልኸኛ ያደርገዋል። ምሕረት ለሮጠ ወይም ለወደደ አይደለም፡ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ።”

95 ስለዚህ፡ ይህ የእናንተ ጉዳይ አይደለም። እናንተ የምታደርጉት አንድም ነገር የለም። ጸጋ ከሆነ፡ ነፃ ስጦታ ከሆነ፡ እናንተ ልታደርጉት የምትችሉት ነገር

የላችሁም። የሰጣችሁ እግዚአብሔር ነው፡ ይህም ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሄር እናንተን አስቀድሞ የወሰነበት ጉዳይ ይህ ነው።

96 መጽሐፍ ቅዱስ ይላል፦ "የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ አስቀድሞ ለልጅነት ለማደጎ ወሰነን።" ስለዚህ፣ እግዚአብሔር መገለጫዎቹን ለማሳየት፣ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፣ በአሳቡ፣ በጉን ባረደ ጊዜ፣ ያኔ እንደነበረ፡ በጉ በታረደ ጊዜ፡ እኛም ከእርሱ ጋር ታረድን። ያኔ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ የበጉ መጽሐፍ በአሳቡ በአእምሮው ውስጥ በነበረ ጊዜ፡ የኔና የናንተ ስሞችም፡ በገዛ ታላቅ አሳቡ ያኔ በመጽሐፉ ውስጥ ተጻፉ።

97 ፍጻሜ የለውም። ባይሆን፡ ይህን ለምን ይፈቅዳል? (እንዳልኩት፡) ከአዳኝ እና ከኃጢአተኛ ማን ይበረታል? የበለጠ ጥንካሬ ያለው የትኛው ነው? ስለዚህ፡ ብርቱው ለደካማው ፍቃድ ይሰጣል፡ ይህም ክብሩን ለማሳየት ብቻ ነው። ሉሲፈርን ባደረገ ጊዜ፡ ዲያብሎስ እንደሚሆን ያውቃል። እርሱ አዳኝ፣ ክርስቶስ መሆኑን ለማሳየት ግን እንዲሁ እንዲሆን መፍቀድ ነበረበት። እንደዚያ እንዲሆን መፍቀድ ነበረበት።

98 ቆይ፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡ "እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ ይደረጋል፡" አይልምን? ታዲያ ስለምን ትፈራላችሁ?

> እንነሳ እና እንስራ፡
> ከልብ ለሚመጣው መከራ
> እንደሚነዱ ከብቶች አትሁኑ! (ተለምናችሁ የምታምኑ ሁኑ።)
> ጀግኖች ሁኑ!

99 ተነስ! የሚለውን ግጥም ህጻን ሳለሁ የሚያጸናኝ አጭር ግጥም ነው። ግጥሙን እወደዋለው፡ እንደሚከተለው ነው፤

> በሮማውያን፡ ንጉሠ ነገሥት ዘመን፡
> አንድ ጀግና ሮማዊ ነበረ፡
> አንድ ፈሪ ከቤተ መንግሥቱ ፊት ሆኖ፡
> እንዲህ ብሎ ሲጮኽ ሰማ፡
> "ኦህ፡ ይህን ሊያናውጥ የሚችል የለምና፡
> በዚህ ምሽግ ውስጥ መሆን ደህንነት አለው ሲል ሰማ!"
> ጀግናው፡ ግን፡ "ኦህ፡ በፍፁም፡"
> "መንገድ እፈልጋለሁ ወይም ራሴ አበጃለሁ አለ!"

100 ይሄ ነው። ትክክል ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘላለምም ያው ነው ብሎ የሚያስተምር ከሆነ... በዚያ ቀን ከዚህ ድንኳን ሰወጣ ቀላል ነገር አልነበረም፣ የሚነግረኝ ሰው ሁሉ **እንዲህ** ትሆናለህ **እንዲያ** ይሆናለህ ይለኝ ነበር። "እንደ አክራሪ ትቆጠራላችሁ፡ ወደ እስር ቤት ትወረወራላችሁ፡ የጤና ተቋማት ሁሉ ይቃወሟችኋል።" እግዚአብሔር ግን ቀጥል አለኝ። መጽሀፍ ቅዱሱም ያው ነው ብሎታል። አሁን ግን ከሰማይ በታች ባሉ ህዝቦች ሁሉ ላይ ሪቫይቫል ተቀጣጥሏል። ለምን? ስለ ተነሳሁ!

እለት እለት ስራህን እንዴት ታሸንፈዋለህ?
ባገኘኸው ሥራ ፈርተሃልን?
ከፊትህ ስላለው ስራ ጸንተህ ትቆማልህ?
አእምሮህ ደክሟልን ባዶ ሆኗልን? (ይህ ነገር አልወደውም።)
ወይስ ከፊትህ ስላለው ስራ ጸንተህ ትቆማለህ፡
ወይስ ፍርኃት ነግሶብሃል?
እንዲህ ከሆነ፡ ቀጥሎ የሚገጥምህን ነገር፡
ይቻላል ብለህ እያሰብክ ታግለህ አሸንፈው።

101 ጽና። በትክክል። እንደ ዳንኤል፡ በልብህ ዓላማ ይኑርህ። ከእግዚአብሔር ጋር ሁን።

102 "ይህ ሁሉ የሆነው የት ነው? እንዴት ተከናወነ? ሰዎችን እንዲህ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? ለመጥፋት ሁሌም ዝግጁ የሆንነው ለምንድነው? ወንድም ብራንሃም፡ አስረዳኝ። ይህ ሁሉ ተጠራርጎ መጥፋት አለበት ብለህ እንድታስብ ያደረገህ ነገር ምንድነው? ከዚህ በፊት በአንቲዲሉቪያን ጥፋት፡ (ልክ ነው? ) አንድ ጊዜ ተጠራርጎ ጠፍቶ ያውቃል። አሁን ጠለቅ ያሉ ነገሮች መጥተዋል። ለማንበብ እንዘጋጅ።

103 አሁን ከእኔ ጋር፡ ወደ ኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 3ኛ ላይ እንድትሻገሩ እፈልጋለሁ። ማንኛውንም ነገር ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ የአምልኮ ሥርዓቶች ሁሉና የርዕዮተ ዓለሞች፣ አሉን የምንላቸው ነገሮች ሁሉ ጅማሬ ከሆነው ከዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ አሳያችኋለሁ። **ዘፍጥረት** ማለት "መጀመርያው" ማለት እንደሆነ ሰንቶች ታውቃላችሁ? በትክክል።

104 ናምሩድ የመሰረታት፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን፡ ባቢሎን ከጅማሬው እናገኛታለን፤ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ መኃሉ ላይ እናገኛታለን፡ በመጽሀፍ ቅዱስ መጨረሻ ላይም እናገኛታለን፤ በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመርያ ላይ፡ የሴቶች ሰባኪዎች ለማስገባት ሰትሞክር፡ እናገኛታለን፤ ይህም ከስራስር የተሰሩትን ትናንሽ ሐውልቶችን በማምለክ ነው። የሂስሎፕ፡ **ሁለቱ ባቢሎኖች፡** ታሪክን ሰንቶች አንብባችኋል? እሺ። በእነዚያ ታሪኮች ውስጥ፡ ፈትሹ። ሴቶች ነበሯቸው... ከዛ በኋላስ፡ ታስታውሳላችሁ? ያዕቆብም የአባቱን አማልክት ሰርቆ፡ ሴት ልጁም ከበታችዋ ደበቀችው ወደ ምድረ በዳም አመጣችው፡ በኋላ ላይ፡ ሰፈሩን ያረከሰው እሱ ነበር። እሺ።

105 አሁን ከዘፍጥረት እናንብብ።

**አባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፡ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ፡** አዝዞአልን? **አላት፤**

**... ሴቲቱም ለእባቡ አለችው፡ በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤**

**ነገር ግን በገነት መካከል... ካለው ከዛፉ ፍሬ፡** እግዚአብሔር **አለ፤** እንዳትሞቱ፡ **ከእርሱ አትብሉ፡ አትንኩትም።**

**እባብም ለሴቲቱ አላት፡ ሞትን አትሞቱም፤**

**ከእርሰዋ** በበላችሁ **ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ** እንደ **እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ፡** (እያችሁ፡ አዲስ መገለጥ ፍለጋ)፡ **እንድትሆኑ፡ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ።**

106 ዛሬስ እነዚህ ሰዎች እንዴት ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመቀነስ እየሞከሩ እንደሆነ እያችሁ? "ለምን፡ እንዲሁ ማፍሰስ፣ ወይም መርጨት፣ ወይም **በዚህ** መንገድ፣ ወይም **በዚያ** መንገድ ማድረጉ፡ ቀላል ነገር ነውን?" ኖ፡ ስር። እግዚአብሔር የራሱ ፕሮግራሙ አስቀምጧል፡ እኛም መከተል ያለብን፡ **እሱን** ነው።

**ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፡** ለዓይንም **እንደሚያስጎመጅ፡ ለጥበብም፡ መልካም እንደ** ሆነ... **እየች** ከፍሬውም **ወሰደችና፡ በላች፤** ለባልዋም **ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርሰዋ ጋር በላ።**

የሁለቱም **ዓይኖች ተከፈቱ፡ እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ... አወቁ፤ የበለሰንም ቅጠሎች ሰፍተው፡ ለእነርሱ** ለራሳቸው **ግልድም አደረጉ።**

107 እዚህ ላይ ለአንድ ደቂቃ ማቆም እፈልጋለሁ። እያችሁ፡ ነገር ሁሉ የየራሱ ጅማሬ አለው። እናንተም ጅማሬ አላችሁ። አሁን... የዚህ ጉዳይ መነሻ አድርጌ ማስቀመጥ የፈለግኩት ነገር ይህ ነው፡ ባለፉት ሁለት ሰብሰባችን ላይ፡ ስለዚህ ጉዳይ፡ ተነጋግረናል።

108 ዛሬ ጠዋት፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ፡ እግዚአብሔር ምድርን ሲሰራ፡ ጋዞችን በሚያበጅበት ጊዜ፡ ጋዞቹ እንዴት ወደ ካልሲየም፣ እና ወደ ፖታሽ፣ እና—ወደ ተለያዩ ነገሮች እንደተቀየሩ፡ በድራማ መልኩ አይተናል። አካላችሁን በመስራት ሂደት ላይ ነበር። እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ፣ እንደ ህንጻ ስራ ፕሮጀክት ተቋራጭ፡ የህንጻውን መሰረት እየጣለ ነበር። አካላችሁን በመስራት ሂደት ነበር፡ በመሬት ላይም አስተኝቶት ነበር። ምን ሊሆን እንዳለ፡ በአእምሮው ውስጥ፡ በትክክል ተረድቶ ነበር።

109 እግዚአብሔር፡ **ይህን** እጅ የሰራው... ዓለምን በሚሰራበት ጊዜ ነው፤ መንፈሴን ግን፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ፈጠራት። ስለዚህ፡ ይህ እጅ እና ይህ አካል ግን፡ ዓለምን በሚሰራበት ጊዜ የሰራው ነው፡ ምክንያቱ ይህ አካል የተሰራው ከአፈር ነው፡ ወደ አፈርም ይመለሳል። እግዚአብሔር ይህን አደረገ። ሁሉንም በታላቁ ንድፍ እና በፕሮግራሙ አስቀምጦታል።

110 አሁን፣ ምድርን ለመሥራት በሄደ ጊዜ፣ ሰውየውን ሠራው፣ ሰውየውም ሙሉ መሰሎ አልታየውም። ይህ ነገር፡ ዛሬ ጠዋት፡ በድራማው ላይ ተመልክተነዋል፡ አባት—ወርዶ፡ በአምሳሉ የተሰራውን ልጁን፡ እንዴት እንዳየው፡ እና የመሳሰሉትን ተመልክተናል። ከዚያም ሚስት አዘጋጀለት፡ ረዳት አደረገለት።

111 አሁን፡ የምድር ፍጥረታትን በሙሉ፡ ስም የሰየማቸው፡ አዳም እንደሆነ፡ አስታውሱ።

112 ከብቶቹንም፣ አራዊትንም፣ ሁሉንም—እርሱ አበጃቸው። ዛሬ ዛሬም፡ እኛ... የዘመን ታሪክ ተመራማሪዎች እና ልዩ—ልዩ ታላላቅ የሳይንስ ባለ

እእምሮዎች፣ ሰው እንዴት በእንስሳ ዝርያ፡ ሊመደብ እንደቻለ፡ ለስድስት ሺህ አመታት ተመራምረዋል... ሰው የእንስሳት ሕይወት ነው። የተሰራነው እንደዛው እንደሆነ፡ እናውቃለን...

113 ሴትም የወንድ አካል፡ የወንድ የአካሉ-ምርት ናት። ሴት በዋናው ፍጥረት ላይ አልነበረችም። ሴቲቱን ከጎን አጥንት እስኪሰራት ድረስ፣ እግዚአብሔር ለብዙ ዘመናት፣ ለዓመታት እና ለዓመታት፡ መፍጠር አቁሞ ነበር። አዳምም ፍጥረታትን በሙሉ፡ እና ሌላውን በሙሉ ሰያሜን ሰጥቶ ጨርሷል፡ ለራሱ ግን ይሄ ነው የማይባል ነበር። በዚህም ምክንያት፡ ረዳት ሰራለት፡ ከጎኑ አጥንት ወሰዶ፡ ጎኑን በስጋ ደፈነ፡ እና ረዳት ሰራለት። ስለዚህ ወንድ፡ በመንፈሱ ውስጥ፡ የወንድ እና የሴት ጾታ ነበረው።

114 ሴት ግን የአንድ ወንድ አካል ነች። አንድ ወንድ ሚስትን ሲያገባ፡ እርሰዋም በትክክል ሚስቱ ብትሆን፡ ከእግዚአብሔር-የተሰጠች ሚስት ብትሆን፡ ስለዚህ ለእሱ ልክ እንደ አካሉ ትሆናለች።

115 በትዳር ውስጥ ብዙ ችግሮች የሚያጋጥሙት በዚህ ምክንያት ነው፡ ምክንያቱ ብድግ ብላችሁ ቡኒ ወይም ሰማያዊ አይን ያላት ቆንጆ ሴት፡ ወይም እንዲት ቆንጆ ኮረዳ፡ ወይም ሌላ ነገር ታያላችሁ፡ ከዛ ትወድቁላታላችሁ። የመጀመርያ ልጇን ሰትወልድ፣ ጥርሶቿ ይረግፋሉ፣ ታረጃለች መጨማደድ ትጀምራለች፡ ከዛ በኋላ ማባረር ያምራችኋል። እናንተ ሴቶችም የእናቱን ግማሽ ቅባት የተመረገ፣ ጸጉሩም ፍሪዝ አድርጎ ለጥ ያደረገ፡ ወጣት ትፈልጋላችሁ። ከልምድ አውቀዋለሁና፡ ሁሉም ይረግፋል። ግን ምን ይፈጠራል? ምንድን ነው? በቃ ትወድቁለታላችሁ።

116 ሴት የአካላችሁ ክፋይ ስለሆነች፡ ከሁሉ በፊት፡ መጸለይ ይገባችኋል። ሴትንም ለአንተ ሚስት አድርገህ፡ ወደ እቅፍህ ወሰደህ እንደ ሆነ፡ እሻራዋም... በደረትህ ላይ ትሰራለች። አንተም እንድታሰተውል እንዲህ እንልሃለን። የእቅፍህ ያልሆነች ሌላ ሴት ከአሻራው ጋር አትመሳሰልም። ለዚህም እግዚአብሔር ይጠይቅሃል። ይህንን እንዳትረሳ።

117 አንተ የሌላ ሰው ሚስት የምትወሰድ ሰው... ዛሬ ከተማ ውስጥ ስለ እንዲት ትንሽ ልጅ ሰምቻለሁ፣ ምስኪን ልጅ። አውቃታለሁ። ይህ ቁማርተኛ ሰው፡ ትልልቅ ልብሶችን፡ እና ዉድ ነገሮችን ስለገዛላት፡ እንዲህ እንዲጫወትባት ነው። እንዲህ አይነቱ ነገር፡ አይጥ እንኳ አታደርገውም፡ እና እንደ ሰው ልትቆጠር አይገባትም።

118 ውሻ እንኳን ይሄን ያህል-አትወርድም፡ እናንተ ግን፡ እናት ውሻን "ልክሰክስ" ብላችሁ ትጠሯታላችሁ። የጄፈርሰንቪል ሴቶች ካላቸው ሞራል ይልቅ የውሻዋ ሞራል ከግማሽ በላይ ይበልጣል። አሮጉትዋ እናት አሳማን "ሶው" ትሏታላችሁ፡ ግን አይደለችም... ከብዙዎች፡ የዩናይትድ ስቴትስ ሴቶች ይልቅ የበለጠ-ሞራል አላት። በትክክል እውነት ነው። እንግዲህ፡ እንደወረደ ነው። በደንብ አደቀዋለሁ ብዬ ግን ነግሬአችኋለሁ፡ ይሄን እንድታውቁት እፈልጋለሁ። ደግሞም እውነት ነው። ዛሬ ያሉ ሴቶች፡ ሞራል ማለት ምን እንደሆነ'ኳን፡ አያውቁም። "ሕሊናዬን አትጉዳ፡" ይላሉ። ከየት፡ ምንም የለሽም። አስተውሉ። የሰ፡ ሰር። ሕሊና'ኮ፡ መልካም እና ክፉ መለየት ማወቅ ነው።

119 አሁን አስተውሉ። ሰውዬው፡ ከተፈጠረ በኋላ፡ እግዚአብሔር መንፈሱን ከፈለ። ከሰውዬውም፡ ከጎኑ፡ ትንሽ አካል ወሰደ፡ ሴት አድርጎ ሰራት። ከዚያም በኋላ የወንዱ ሴታዊ መንፈስ፡ ዉብ የሆነው መንፈስ ወሰደ፡ ሴትን ፈጠረ። ሰውየውንም ተባዕት አደረገው።

120 ታውቃላችሁ… ወ—ወ—ወንድ ሆኖ፡ ጥፍሮቹን፡ ማኒኩር የሚሰራ፡ እንደምታውቁት፡ እና፡ ደግሞ፡ ጸጉሩን በአንዱ በኩል አራት—በሌላኛው አምስት ጎንጉኖ፡ ወደ ታች የሚያወርድ፣ አፉንም ከፍቶ ከፊትሽ የሚቆም፣ ወዘተረፈ፡ ከቆንጆዎቹ ወንዶች አንዱን ካየሽው። እህቴ ሆይ፡ ችግር ያላት ወፍ መሆኗን፡ አትርሺ። ችግር አለበት። ብትጠነቀቂ ይሻልሻል።

121 አንተም ደግሞ ቱታ ለብሳ፡ አፏ ውስጥ ሲጋራ የሰካች ሴት ካየህ፡ “ወዳጄ፡ ምን እንደሆነ፡ ልንገርህ!” ስትልህ ካየኃት፤ ወንድሜ፡ እችን አሮጌት ተጠንቀቅ። ችግር አለባት።

122 ሴት፡ እንደ ሴት መሆን አለባት፡ እንደ ሴትም ትልበስ። እግዚአብሄር ወንድን ሲያበጀው፡ አንድን ነገር እንዲሆን ነው፡ ሴትንም ሌላ ነገር እንድትሆን አበጃት። እግዚአብሔር ወንዱን ሲያለብሰው በአንድ መንገድ፣ ሴቲቱም በሌላ መንገድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም “ለሴት የወንድን ልብሰ መልበሰ አስጸያፊ ነው፡” ይላል።

123 እናንተ ሴቶች፣ እነዚህን ብጣሽ ሱሪዎችን እና አሸንክታቦችን ለብሳችሁ፡ የነተቡ፡ ነገሮችን ለባብሳችሁ… ሰሙ ማን ነበር፡ ኒከርቦከር ነው? ማን ነበር የሚሉት… ? ኦህ፡ ያንን ተራ ነገር… ? ኖ፡ ኖ፡ ቁምጣ አይደለም፡ ሌላኛው፡ ረጃጅም እግር አለው። [አንድ ሰው “ፔዳል ፑሽር፡” ብሎ ተናገረ።—አርታዒ።] ፔዳል ፑሽር፣ እና ቱታ፣ ዳንጋሪስ።

ቀጥሉ፡ “የሴቶች ነው፡” ይባላል።

124 እኔ እላችኋለሁ፡ “ፍጹም፡ ሰታችኋል። እመቤቶች ይህን አይለብሱም። ለሴት ምናልባት፡ ለወይዘሮ ግን አይሆንም።” አዎን።

125 መጽሐፍ ቅዱስም ይላል፦ “ለሴት የወንድን ልብሰ… ለወንድም የሴትን ልብሰ መልበሰ አስጸያፊ ነው።”

126 ወንዱ በየቀኑ ሴታ ሴት እየሆነብን መጣ፡ ሴቶችም፡ ወንዳ ወንድ እየሆኑ መጡ። ምንድነው ችግሩ? ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከመጽሐፍ ቅዱስ፡ እናውቀዋለን። ሴቶች ከእንግዲህ ሴቶች አይደሉም። እናንተ ክርስቲያን ሴቶችን ማለቴ አይደለም። ስለ አጠቃላይ ሁኔታ እያወራሁ ነው። እንደ ወንዶች መሆን ይፈልጋሉ ፀጉራቸውን እንደ ወንዶች መቁረጥ ይፈልጋሉ፡ እጃቻቸውን ባር ላይ **እንዲህ** ሰቅለው፣ ከአፋቸው ሲጋራ ሰክተው፡ **እግዚአብሔር አሜሪካን ይባርክ** ይዘምራሉ።

127 አውራው ጎዳና ላይ ተመልከቱ፡ መንገድ መኃል፡ እንዲሁ ያቆማሉ። ቆጥረናቸው… አንድ ነገር ልንገራችሁ። እናንተ ሴት ሹፌሮች፡ አድምጡኝ። እኔ እና ቢሊ ፖል፣ ለሰድሰት ወራት፣ በአገሪቱ በነበረን የመጨረሻው ካምፔን፣ መንገድ ላይ ሰንት የተገለበጡ እየቆጠርኩ ነበር። መንገድ ላይ፡ ከሦሰት መቶ ጥፋቶች ውስጥ፣ ከመካከላቸው ሰንት የሴት ሹፌር ቢሆኑ ጥሩ ነው? ሌላ የለም ማለት ይቻላል… አሰራ ዘጠኙ ብቻ ወንዶች ናቸው። እና ሁለት መቶ

ሰማንያ፡ ወይም ሁለት መቶ ሰማንያ-አንድ ይመስለኛል፡ ሴት ሹፌሮች ናቸው። ሴት ሹፌሮች! አሁን፡ ይሄን ስናገራችሁ ጎበዝ ሴት አሽከርካሪዎች የሉም ማለቴ አይደለም። ይሁን እንጂ ማስናከሏ አይቀርም።

128 እስኪ ወደ እሷ ለመቅረብ ሞክረሃልን? የደሰደሰ ያላት፣ ዝምተኛ፣ ትራፊኩ ሲመጣ ጸጉሯን ወደ ላይ ዘርዘር የምታደርግ ከሆነች። “እንዴ፡” “በርግጥ፡ ጥፋት አጥፍተሻል!” እህህም! ነገር ግን ህጉ ገና አልጸደቀም፡ ይላታል።

129 በቅርብ ጊዜ ከተላቀቅኩት የግብር ቅጣት እየመጣሁ ሳለሁ ራሱ አረጋግጠውልኛል። ህጉ ገና አልጸደቀም። እንግዲያውስ...

130 የእንግሊዝ ታላላቅ መኳንንት “ዴሞክራሲ መልህቅ የሌለው ተጓዥ ነው፡” ማለታቸው ምንም አያስደንቅም። ትክክል ነው፡ በምርጫ ቅስቀሳ፡ ሳጥን ላይ ይቆማሉ። ዴሞክራሲ በሰብሷል፡ ዲክታተሮች እና ሌሎቹም ያው ናቸው። ነገሩ ሁሉ የበሰበሰ ነው። እግዚአብሔር ሁሉንም አጥፍቼ፡ በአዲስ መልክ እጀምራለሁ እንዳለ፡ መላ ነገሩን ከመደምሰስ በስተቀር፡ የሚያደርገው ሌላ የለውም። መምጣቱ ምን ያህል እንደቀረበ ተመልከቱ።

131 አሁን ሴቲቱን... ረዳት ባደረገላት ጊዜ፣ ረዳት እንድትሆነው ነበር። ከዛ...

132 እዚህጋ፡ ከኔ ጋር የሚስማማ አንድ ሰባኪ፡ ገጥሞኝ አያውቅም። በሌላ መንገድ ሊያብራሩት ይሞክራሉ፡ ለእኔ ግን ትርጉም አይሰጠኝም። አዳም እና ሔዋን አፕል በሉ ማለት ይሞክራሉ። ወንድሜ፡ ለመቀለድ ፈልጌ አይደለም... ይሁን እንጂ፡ መናገር አለብኝ። አፕል መብላት ሴቶችን ራቁታቸው መሆናቸውን እንዲገነዘቡ የሚያደርጋቸው ከሆነ፡ አሁን ብናከፋፍላቸው መልካም ነው። ልክ እንደሆነ እናንተም ታውቃላችሁ።

133 ታውቃላችሁ፡ እራቁታቸው መሆናቸውን እንዲያውቁ ያደረጋቸው፡ አፕል መብላት፡ አይደለም። እውነት እላችኋለሁ፡ አይደለም። ጉዳዩ ወሲባዊ ንክኪ ነው። መሆንም አለበት፡ ምክንያቱ የተከለከለውን ዛፍ በበሉ ጊዜ እራቁታቸው መሆናቸውን አወቁ። ሴት ፍሬ የምታፈራ ዛፍ አይደለችምን? እናንተስ የእናታችሁ ፍሬ አይደላችሁምን? እንዳይወሰድ የተከለከለው ፍሬም ይህ ነበር።

134 አሁን እዚህ ጋር አንድ ትልቅ ነገር አለ። ሳይንስ የሰው ልጅ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ በጣም የቀረበበት ሰራው... አጥንቶችን ቆፍረው፣ ቅሪተ አካላትን ሰብስበው፣ ራስ ሰብስበው፣ ቅል ሰብስበው፣ እጆችን፣ አጥንቶችን ይሰበስቡና፣ እንደ ሰው ለማስመሰል ይሞራሉ። ስለ ሰው ልጆች ተመራምረው፡ ወደ ሰው ቅርብ ሆኖ፡ ያገኙት ነገር፡ ቺምፓንዚን ነው። ለሰዎች ልጆች እጅግ ቅርብ ሆኖ ያገኙት ዝርያ ይህ ነው፡ በዚህ ሁሉ ግን ከሰዎች ልጆች ጋር፡ ምንም ጉዳይ የለውም።

135 በጣም ዝቅተኛው የሕይወት ዝርያ እንቁራሪት ሲሆን፡ ከፍተኛው ዝርያ የሰው ልጅ ነው። እግዚአብሔርም ከታች ጀምሮ፡ የአምሳሉ ቱንቢ እስኪያመጣ ድረስ ወደ ላይ መጣ። ወደ እግዚአብሔር አምሳል እስኪያደርሰው ድረስ በአእዋፍና በአራዊት አለፈ፣ ወደ ላይም ወጣ። ሰውን በዚያ መልክ ፈጠረ። ከፍተኛው ዝርያ እሱ ነው። ዝቅተኛው ዝርያ ወደ እንቁራሪት፡ እና ወደ ሌላ ነገር እየተለወጠ የሚያድግ ትል ነው።

136 አሁን፡ ሊደርሱበት ያልቻሉት፡ የተሰወረባቸው አገናኝ አለ። አሁን ቃሉን ተከታተሉ። እናንተ፡ ብዙዎቻችሁ፡ ከዚህ ጋር አትስማሙም፡ ይሁን እንጂ… እንድትይዙት ብቻ እፈልጋለሁ። እንዲሁ በጭፍንነት አትጣሉት። አድምጡኝ።

137 ብዙዎቻችሁ ዶክተር ዲሀንን እየሰማችሁ እንደነበራችሁ አውቃለሁ። እኔ በርግጠኝነት እላለሁ… ድንቅ ችሎታ እንዳለው አንድ ሰው፡ እና እንደ ባፕቲስት ወንድምነቱ፡ በርግጠኝነት አደንቀዋለሁ። ከማንም የተሻለ እእምሮ እና ብሩህነት አለው፤ እና—እኔ ከማውቀው በላይ ያውቃል፤ ምክንያቱ የስነ—መለኮት ምሁር ነው፣ ሜዲካል ዶክተር ነው፣ እንዲሁም የሳይንስ ዶክተር ነው። ብልህ ሰው ነው። ስለ ኔፍሊሞች ሲናገር ግን… የእግዚአብሄር ልጆች የሰው ሴቶች ልጆች መልከ መልካም መሆናቸውን ባዩ ጊዜ፤ “ራሳቸውን—ወደ ሰው ሥጋ በመግባት፡” ለራሳቸው ሚስቶችን ወሰዱ፡ በኖድ ምድርም ኔፍሊሞች ነበሩ። በማለት የጆሲፈስን አቋም ይይዛል። “የእግዚአብሔር ልጆች፡ የወደቁ መላእክቶች፡ የሰውን ሴቶች ልጆች አይተው፣ ሚስቶች እንዲሆኗቸው ከወሰዷቸው በኋላ፣ ከመውደቃቸው የተነሳ፡ የወሲብ ጥማታቸው እጅግ ከፍተኛ ስለነበረ፡ እራሳቸውን ወደ ሰው ስጋ አስገቡ።”

138 ይህን’ማ ካደረጉ መለኮታዊ ፈውስ ያበላሹታል፡ ሌላውን ሁሉ ያበላሹታል። ዲያቢሎስ መፍጠር አይችልም። ዲያቢሎስ መፍጠር ከቻለ’ማ፡ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነው። እስኪ ሰይጣን መፍጠር የቻለበት አንድ ቦታ አሳዩኝ። የተፈጠረውን ብቻ የሚያጣምም ነው እንጂ። መፍጠር አይችልም። አጣማሚ ነው እንጂ። ፈጣሪ አይደለም።

139 እሺ፡ ከዛ በኋላስ፡ ምን ተፈጠረ? ተከታተሉ። እኔ የምለው ይኸው ነው። የጠፋው ማስርያ ይህ ነው።

140 እነሱ ቺምፓንዚን ይጠቅሳሉ፡ ይሁን እንጂ ቺምፓንዚን ከሴት ጋር ብታዳቅሉት ልጅ መውለድ አይችልም። ሰውን ከማንኛውም እንስሳ ጋር ማራባት አይቻልም። አይቀላቀልም። የማንኛውንም እንስሳ ደም፡ መጠቀም አትችሉም።

141 እኔ አፍሪካ በነበርኩበት ጊዜ፡ ምስኪኑን ጥቁር ህዝብ፡ በዚህ መንገድ ሲያራክሷቸው አይቻለሁ፤ አንድ ሰው፡ “ከእንስሳ አይሻሉም፡” አለኝ።

142 እና እንዲህ አልኩት፦ “ይኸውልህ። ልክ እንደ አንተ ሰዎች ናቸው፡ ምናልባትም ከአንተ የተሻሉ።” ልንገራችሁ፡ እንደዚህ አይነት አመለካከት ሲኖራችሁ፡ እንስሳ ወደ መሆን እየተመለሳችሁ ነው። እንዲህ አልኩት፦ “ይህ ሰው፡ እንደ ካርታው ጦር የጠቆረ ቢሆንም፣ እንደ ዱባ ቢጫ ቢሆንም፣ ወይም እንደ ኢንዲጎ ሰማያዊ ቢሆንም፡ ደሙን ለግሶ ህይወትህን ሊያተርፍ ይችላል። የእንስሳትን ደም ግን በጭራሽ አትጠቀምም።” እሱ በትክክል፡ ሰው ነው።

143 የአንዱ ቆዳ ጥቁር፣ የሌላው ቡናማ፣ ሌላኛው ቢጫ የሌላው ነጭ ስለሆነ ብቻ፣ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። መጽሀፍ ሲናገር “እግዚአብሔር ከአንዱ ደም ሰውን ሁሉ አበጀ፡” ይላል። ይህም በትክክል እውነት ነው። የምንኖርባቸው ቦታዎች፡ ቀለማችንን በመቀየራቸው፡ ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም። እግዚአብሔር—ከአንዱ ሰው ሰዎችን ሁሉ፣ ህዝቦችን በሙሉ፡ ከአንድ ፈጠራቸው።

144 ጥቁሩ ሰው፡ ቻይናዊውን እንዲህ ሊለው አይገባም፡ ጥቁሩ ሰውም ቻይናዊውን፦ ማለት “ይህ ቻይናዊ፡ ቢ—ቢጫ ነው፡ ከሱ ጋር ምንም ጉዳይ

የለኝም፡” አትበል። ወንድምህ ነው። አንተም ነጭ ሰው ሆይ ቢጫውን ወይም ጥቁሩን፡ ወይም አንዳቸውን “ከአንተ ጋር ምንም ጉዳይ የለኝም፡” አትበለው። ወንድምህ ነው። በትክክል እውነት ነው።

145 አስተውል፣ አሁን፣ የሆነው ነገር ይኼ ነው። ይኼን ያደረገው እባቡ እንደሆነ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አስደግፌ፡ አምናለሁ። በቺምፓንዚው እና በሰውየው መካከል የተሰወረው አገናኝ እባቡ ነው። ምክንያቱ፡ አሁን ይሄን ሰሙኝ፡ አዳምጡኝ፡ እባብ ተሳቢ አልነበረም። ከምድር አራዊት ሁሉ፡ ይልቅ “ተንኮለኛ” ነበረ።

146 ዛሬ፡ **ተንኮለኛ** የሚለውን ቃል፡ ምን ማለት እንደሆነ፡ በተለያየ መልኩ ለማወቅ፡ ዲክሺነሪ ከፍቼ፡ እየመረመርኩት ዋልኩ። ይህ ማለት “ብልህ፣ ጥበበኛ መሆን ነው፣” ሌላው፡ የዕብራይስጡ—ትክክለኛ ትርጓሜ (ከ ማኃህ ኤም-ኤ-ኤች-ኤ-ኤች ነው) “ስለ ሕይወት መርሆዎች ትክክለኛ እውቀት ያለው” ማለት ነው።

147 አሁን ለአንድ ደቂቃ ብቻ ይህንን እንመልከት። እባቡ ብልህ፣ ጥበበኛ ነበር፣ መጠርያው ግን “እባብ” ይባላል። ከሌሎች ሁሉ ይልቅ፡ ብልህ እና፡ በምድር ካሉ ሌሎች ሁሉ ይልቅ፡ በምስሉ እጅግ ሰውን የሚመስል፡ ወደ ሰው ልጆች እጅግ የቀረበ፡ እንደነበረ ይሄን አትርሱ። እየተሳበ የሚሄድ እንስሳ አልነበረም። በሆዱ እንዲሳብ ያደረገው እርግማን ነው። መጽሀፍ ስለሱ ሲናገር… ከሌሎች ሁሉ ይልቅ ውብ ነበር ይለዋል።

148 እርግማኑ አሁንም እንኳን ውበቱን ሁሉ አልወሰደም፤ የእባብ ድንቅ ቀለማት፣ ሞገሱ እሰሰትነቱ፣ አሁንም ድንቅ ናቸው። መርገም እንኳን አላሰወገደበትም። እግሮችህ ይወገዳሉ በሆድህም ትሄዳለህ፡ ብሎ እግዚአብሄር እንደተናገረው፡ አስታውሱ። በእባብ ሰውነት ውስጥ የሰው ልጆች የሚመስል አንድ አጥንት ማግኘት አትችሉም፡ ሳይንስ የተሸወደበት ምክንያትም ይህ ነው። እሱ እንዲሁ ነው።

149 እግዚአብሔር ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ዓይን ሰውሮ፡ የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች በሚገለጡበት በዘመኑ ፍጻሜ፡ ለእግዚአብሔር ልጆች ይገልጥላቸው ዘንድ፣ “ዓለም ሳይፈጠር በፊት በደስታ ዕልል ያሉትን የእግዚአብሔርን ወንዶች ልጆች፡” ቃል ገብቶላቸዋል። የታላቁ ምልአተ መለኮት እና የሌሎቹ ትምህርቶች መገለጥ በሚዘንብበት በዘመን ፍጻሜ፣ እነኚህን ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች በኩል ይገልጸዋል። መጽሀፍም እንዲህ እንደሚያስተምር ታውቃላችሁ። ስለዚህም እዚህ ተገኘን። ጌታ እነዚህን ነገሮች ለእኛ እየከፈታቸው ያለበት ምክንያትም ይህ ነው። እግዚአብሔር ልጆቹ እንዲገለጡ እያደረጋቸው ነው። ከሰው የእውቀት ልክ አልፎ፡ ወደ ውስጠኛው መንፈሳዊ መገለጥ ውስጥ ዘልቆ በመግባት፡ አሁን እያወረደው ይገኛል። በመጽሀፍ ቅዱስ፡ “እነሆ ጥበብ ላለው፡” የሚለውን አላስተማርንምን? በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክኮ የተማረውን እና እግዚአብሔምር እንዲሰጠው የወደደውን እንጂ፡ በሴሚናሪዎች የተማረውን አይደለም። የእግዚአብሔር ልጆች፡ መገለጥ!

150 እነሆ እባቡ፡ አሁን እባቡ ምን እንደነበረ፡ ስለ'ሱ ያለኝን ዝርዝር መረጃ እሰጣችኋለሁ።

151 ከታችኛው... ከትሉ ተነስተን፡ ከእንቁራሪት ጀምረን፡ **ይሄኛው-እና-ያኛው**፡ እያልን፡ እስከ መጨረሻው ዝንጀሮ፣ እስከ ቺምፓንዚው ድረስ፡ ደርሰናል። አሁን ደግሞ ከቺምፓንዚው፡ ከቺምፓንዚው ተነስተን ሰው ልጅ ደረስን፡ ከዛ ጥያቄ ይሆንብናል።

152 "እንግዲህ፡" ሳይንስ፡ "ቆዩ አሁን! ሴትዋን ከዝንጀሮ ጋር ከፓንዚ ጋር፣ ወይም በተቃራኒው፡ ሰው ከቺምፓንዚ ጋር ማዳቀል እንችላለን" ይላል። አይሳካም። ከሌላ እንስሳ ጋር ማዳቀል አይቻልም። ደሙ አይቀላቀልም፡ ደማችሁን ብታስተያዩ፡ ሙሉ በሙሉ ይለያል፡ ሙሉ በሙሉ።

153 በዚህ መካከል ግን የሆነ ደም ይታያል፡ እንሰሳውን ማወቅ ግን አልቻሉም። ኦህ፡ ሀሌ ሉያ፡ አሁን መንፈሳዊነት ሊሰማኝ ጀመረ። ተከታተሉ። ለምን? እግዚአብሄር ሰለ ደበቀባቸው። በእባብ ውሰጥ የሰው አጥንት የሚመስል አጥንት የለም። ጥበበኞች ተመራምረው እንዳይደርሱበት ነገሩን በጣም ሩቅ አድርጎ ሰወረው።

154 እኔ ደግሞ ዛሬ ይህ ጥበበኛ ሰው ከየት እንደመጣ፡ እንደው አሁን፡ የ—የት እንዳለ፡ አሳያችኋለሁ። እያችሁ፡ በዛ መንገድ አትደርሱበትም።

155 በመገለጥ መምጣት አለበት፡ "አንተ ክርሰቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ... " "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርሰቲያኔን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።" በመንፈሳዊ መገለጥ። አቤል እንደ ቃየል የሜዳውን ፍሬ ከማቅረብ ይልቅ፡ ጠቦት ማቅረብ እንዴት—አወቀ? በመንፈስ ተገለጠለት። በሴሚናሮች አታገኙትም። በሐይማኖት ተቋም ውሰጥ አታገኙትም። ከሰማይ ግን ታገኙታላችሁ።

156 አሁን እባቡን ተመልከቱት፡ ይህ ከመጀመርያ የነበረው እባብ ነው። አሁን ምስሉን እንሳል። በሰው እና በቺምፓንዚ መከካል ነው። ዘለግ ያለ ወጣት ነው። እና፡ እባቡ፣ ዲያብሎስ፣ ሉሲፈር ሊጠቀምበት የሚችል፣ ደሙ ከሰው ደም ጋር ሊቀላቀል የሚችለው ሰው፣ እሱ ብቻ መሆኑን አውቋል። የቺምፓንዚ ደም ሰለማይቀላቀል፡ እሱን መጠቀም አይችልም። ሌሎች የተለያዩ ነገሮችን መጠቀም አይችልም። በግን መጠቀም አይችልም። ፈረሰን መጠቀም አይችልም። እባቡን ከመጠቀም በቀር፡ በሌላ የትኛውም አይነት እንሰሳ መጠቀም አይችልም።

157 አሁን እንያዘው እና ምን እንደሚመሰል እንመልከተው። የጥንቱ ዘመን ግዙፍ፡ ታላቅ ግሩም ወጣት ነው። ትላልቅ አጥንቶች የሚያገኙ ለዚህ ነው፡ እና ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳያችኋለሁ። በደንብ ተከታተሉኝ። እሺ። ይህ ታላቅ ግሩም ፍጥረት፡ ባለ ታላቅ ግሩም ትከሻ፡ ቁመቱ—አሥር-ጫማ ነበር እንበል፡ ልክ ሰው ይመሰል ነበር። ደሙም፡ ከወረደ በኋላ፡ አንዱ እንሰሳ ከሌላው ጋር ሲዳቀል፡ እንሰሳትን ማዳቀል ይቻላል፤ እና ወደ ሰዎች አድማስ፣ ከፍ ወዳለው ህይወት፣ ከፍ ያለ ዝርያ፣ እስኪደርስ ድረስ ደማቸውም ከፍ እያለ ይሄዳል። በዚህ መካከል ግን፡ እዚህ ጋር የነበረው ኮኔክሽን፡ ተቋረጠ። ሳይንስ የጎደለውን ማሰርያ ማግኘት እንደማይቻለው ሰንቶች ታውቃላችሁ? ሁላችሁም ታውቃላችሁ። እንዴት? እነሆ፡ እባቡ። እነሆ፡ ታላቅ እና ግሩም ወጣት ነበር።

ዲያብሎስም ወረደና፡ አሁን፡ "አብርሆት መሰጠት እችላለሁ፡" አለ።

158 አሁን፡ የሴት ድርጊቶቿ እና ሁኔታዋን ለማየት ስትወጡ፡ አስታውሱ፡ (ሚስታችሁ አይደለችም) ስለዚህ በዲያብሎስ ተቀብታችኋል።

159 አሁን፡ ተከታተሉኝ፡ ዲያብሎስ ወርዶ ወደ እባቡ ዘንድ ገባ። ሄዋንም በገነት ዛፎች፡ እራቁቷን ሆና አገኛት፡ በመኃል ላይ ስለሚገኝ ፍሬም ያጫውታት ጀመር። **ሚድስት** ማለቱ "መኃል፡" ማለት ነው፡ መቼም በተቀላቀለ ጉባኤ ውስጥ፡ እናንተ ይገባችኋል። እርሱም፡ "አየሽ፡ አስደሳች ነው። ለማየትም ያማረ ነው፡" አላት። ምን አደረገ? ከሄዋን ጋር ወሲብ አደረገ፡ ከእሷም ጋር፡ እንደ ባል ኖረ።

160 እርሷም ደስ የሚያሰኝ እንደሆነ አይታ፡ ወደ ባልዋ ሄዳ ነገረችው፡ ይሁን እንጂ ከሱ በፊት፡ በሰይጣን ፀንሳ ነበረች።

161 የበኩር ልጅዋን፡ ቃየን የተባለውን የሰይጣን ልጅ፡ ወለደች።

"አሁን፡" "ይህ ስህተት ነው፡" ትላላችሁ።

162 እሺ፡ ልክ ይሁን ስህተት አሁን እናረጋግጣለን። "በዘርሽ እና በእባቡ ዘር መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ።" ምን? የእባብ ዘር! እሷ ዘር አላት፡ እሱም ዘር አለው። "እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፡ አንተም ስኮናውን ትቀጠቅጣለህ።" እዚህ ጋር፡ **መቀጥቀጥ** ሲል "ስርየትን ማድረግ፡" ማለት ነው። ይኸው የእባቡ "ዘር" ይኸውላችሁ።

አሁን፡ አስተውሉ፡ ሁለቱ ሰዎች የመጡበት ይህ ነው።

163 አሁን፡ ይህ እባብ፡ በመጣ ጊዜ፡ ይህ ታላቅ እና ግሩም ወጣት ወደሷ በቀረበ ጊዜ፡ ከአዳም ሚስት ጋር በማመንዘር ጥፋተኛ ተባለ። ዛሬ ኃጢአት የት አለ? ነገሮች ዛሬ እንዲህ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድን ነው? አሁን፣ በእርግጠኝነት እኔ—የማ... የማወራውን ነገር መረዳት ትችላላችሁ። እና ያ ነበር።

እርሱም ይህን ባደረገ ጊዜ፡ እግዚአብሄር፡ አዳምን እና ሔዋንን መጥራት ጀመረ።

እርሱም "ራቁቴን ነኝ፡" አለ።

እርሱም "ራቁትህ እንደሆንክ ማን ነገረህ? " አለው፤

164 እና እንደ ጦር ስራዊት ባህርይ፡ ማላከክ፡ ጀመሩ። "አይ፡ አንተ የሰጠኸን ሴት፡ እንዲህ አረገችኝ። እሷ ናት ያሳመነችኝ፡" አለ።

165 እሷስ "እባቡ አፕል ሰጠኝ" አለች? እሺ፡ ሰባኪ ሆይ፡ ወደ ቀልብህ ተመለስ።

166 "እባቡ አታለለኝ፡" አለች። **አታለለኝ** ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? "አበላሸኝ" ማለት ነው። እባቡ... ለእሷ... እባቡ-... ዲያብሎስ አፕል አይሰጣትም። "እባቡ አታለለኝ።"

ከዚያ በኋላ እርግማኑ መጣ።

167 እርሱም እንዲህ አላት፡- "ባልሽን ከመስማት ይልቅ እባቡን ስለሰማሽ፡ ህይወት ከዓለም አስወገድሽ። ጭንቅሽም እጅግ—እጅግ ታበዣለሽ፤ ፈቃድሽም በባልሽ ላይ ይሆናል፡" እና ሌላ ሌላ ተናገራት።

168 “አንተም እኔን ከመስማት ይልቅ፡ ሚስትህን ስምተሃልና (ከአፈር አንስቼ፡ ታላቅ ዝርያ አድርጌህ ነበር)፡ ወደ አፈር ትመለሳለህ።”

169 “አንተም፡ እባብ፡ ይህን ስላደረግክ፡ እግርህ ይጠፋል። ዘመንህ በሙሉ፡ በሆድህ ትሄዳለህ። ሌሎች ይጠሉሃል። ምግብህም የምድር አፈር ይሆናል።” ይሄው ነው። የጠፋው ማስርያ ይህ ነው።

170 እነሆም ቃየን መጣ። ባህርይውን እንመርምረው። ቃየን ሲመጣ። እንዴት ነበር? ብልጥ ነጋዴ ነበር። እርሻውን ያርሳል። ብልህ፣ አስተዋይ፣ ሐይማኖተኛ፣ በጣም ሐይማኖተኛ ነበር፣ አሁን ተመልከቱ—ባህርያቶቹን ተመልከቷቸው። ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ከእኔ ጋር ተጓዙ።

171 እነሆ መጣ። ሰነ ምግባር እንዳለው ያውቃል። ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ይፈልጋል። ቸርች ሠርቶለታል፡ መሰዋዕት አቅርቦለታል። መሠዊያ ሰርቷል፡ እና ሁሉንም አድርጓል። መሠዊያን ሰርቶ አበቦቹን በላዩ ላይ አኑሯል። የእርሻ... የእርሻውን ፍራፍሬዎች፡ ለእግዚአብሔር ሰውቷል። “ይኸው፡ ጌታ ሆይ፡ የችግሩ ምክንያት አፕል እንደሆነ ገብቶኛል፡ ለዚህ ነው የምንበላው፡” አለ። አንዳንድ ተከታዮቹ ተመሳሳይ አመለካከት አላቸው። ከየት እንደመጡ ያሳያል። አፕሎች፡ ከማሳው ለቀመ፡ እና በመሰውያው ፊት አቅርቦ፦ “የሐጥያት ሰርየት በዚህ ይሆናል፡” አለ።

እግዚአብሔርም “አፕል አይደለም፡” አለ።

172 ነገር ግን፣ በመንፈሳዊ መገለጥ፣ አቤል ደም መሆኑን ተረዳና። በግ አምጥቶ፡ አንገቱን ቀጨው፡ በጉም ሞተ።

173 እግዚአብሔርም “ትክክል ነው። በዚህ ነው። የመጣው በደም ነው፡” አለ። ስለየትኛው ደም እንዳልኩ ታውቁታላችሁ። እሺ። “ይህን ያደረገው ደም ነው።”

174 አሁን ተከታተሉኝ። ቃየን ወንበር-ሰባሪው ወንድሙ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን፣ በዚያም ምልክትና ድንቅ መደረጉ ባየ ጊዜ፡ ቀናበት። “እነዚህን ነገሮች አሁን ማስቆም አለብን፡” አለ። ዛሬም፡ ወንድሞቹን ተመልከቷቸው፣ ልጆቹንም ተመልከቷቸው። “እንዴ፡ ከሱ ይልቅ እኔ ብልህ ነኝ፡” አለና ተቆጣ። **ቁጣ** ከየት መጣ? ቁጣው ነው ትላላችሁን... ? ወንድሙን ገደለ። ነፍስ ገዳይ ነበር።

175 እግዚአብሔር ገዳይ ነው ማለት ትችላላችሁን? አዳምም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። መጽሐፍ ሲናገር፡ ያኔ በንጹህ ጅምር ላይ፦ “አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፡” ይለዋል። አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። ያ ቅናት ምቀኝነት እና ሌላው ነገር ሁሉ፡ ከዚያ ንጹህ ምንጭ ሊወጣ አይቻለውም።

176 የወጣው ከሌላ ሰፍራ መሆን አለበት። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] የወጣውም ከመጀመርያ ጀምሮ፡ ገዳይ ከነበረው፡ ከሰይጣን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ “እሱ ከመጀመርያ ጀምሮ፡ ውሸታም እና ገዳይ ነበር፡” ይለዋል። እነሆ። ወንድሙንም ገደለ።

177 ይህም የክርሰቶሰ ሞት ምሳሌ ነው። ከዚያም፣ በዛ ውሰጥ፣ ቦታውን እንዲተካ፣ እርግጥ፡ ሴትን አሰነሳ። የክርሰቶሰ መሞት፣ መቀበር እና ትንሳኤ ነበር።

178 ተከታተሉኝ፡ ከዛ በኋላ፡ ቃየን ወደ ኖድ ምድር ሄደ። ግዙፎቹም ያን ጊዜ መጡ። አባቱ ታላቅ እና ግዙፍ ሰው ከነበረ፡ ቃየን ማንን ሊመስል ይችላል? አባቱን። ወደ ኖድ ምድርም ሄደ፡ ከእኅቶቹም መካከል አንዷቱን ወሰደ።

179 ሊሆን የሚችለው ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። ሴቶቹም ከሔዋን ካልሆነ በቀር፡ የሚመጡበት ሌላ መንገድ የለም። ሰባ ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንደነበራቸው ይነገራል። ሴቶች ባይኖሩ—ኖሮ... መጽሐፍ ቅዱስ የተወለዱ ሴቶች አይቆጥርም፡ ወንዶች ብቻ። ከሔዋን ሌላ ሌሎች ሴቶች ባይኖሩ ኖሮ፣ እሷ በሞተች ጊዜ፣ የሰው ዘር በጠፋ ነበር። ሴቶች ልጆች ወልዳለች። እሱም የገዛ እህቱ ማግባት ነበረበት።

180 ሚስቱን ይዞ—ወደ ኖድ ምድር ሄደ። በዚያም እሷን ባገባት ጊዜ፡ እነኚያ በአባታቸው፡ በዲያብሎስ፡ በቃየን በኩል የመጡ ታላላቅ፣ እና ግዙፎች ያገኙ፡ በዚያ ነበር። የጠፋባችሁ ማስርያም ይህ ነው።

181 አሁን የእባቡን ዘር ተመልከቱት። አሁን ተከታተሉ። አስታውሱ፡ የእባቡ ዘር ሐይማኖተኛ ነው። አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች፡ ሲንቀሳቀስ ተመልከቱት። የእባቡ ዘር፡ እነሆ ጀመረ። ምን ገጠማቸው? አሁን አንድ ነገር ላንብብላችሁ፣ ዛሬ ከሰአት በኋላ የጻፍኩት ነው።

182 የአቤል ዘር ሐረግ ተከትሎ ማን መጣ? ይሄን አድምጡኝ። በጣም ጥሩ። አቤል መጣ። ከአቤል በኋላ ሴት መጣ። ከሴት በኋላ ኖህ መጣ። ከኖህ ሴም መጣ። ከሴም አብርሃም መጣ። ከአብርሃም በኋላ ይስሐቅ መጣ። ከይስሀቅ በኋላ ያዕቆብ ተወለደ። ከያዕቆብ ይሁዳ መጣ። ከይሁዳም ዳዊት መጣ። ከዳዊት በኋላ ክርስቶስ መጣ፡ ወደ ፍጹምነት ደረሰ።

183 የእግዚአብሔር መንፈስ በአቤል ዘንድ እንዴት እንደኖረ ተመልከቱ። በሴት ውስጥ እንዴት እንደኖረ ተመልከቱ። በይሁዳ ውስጥ እንዴት እንደኖረ ተመልከቱ። በዳዊት ውስጥ እንዴት እንደኖረ ተመልከቱ። ያው አንዱ መንፈስ፡ በጻድቃን ዘር በኩል፡ እስከ ታች ድረስ ሲጠራ ተመልከቱ። ምንም ቢያደርጉ፡ አስቀድመው የተወሰኑ ናቸው።

184 ያዕቆብ እዩት፡ የቆሸሸ... ይህን ስናገር ከክፋት አይደለም። ያዕቆብ ግን፡ ትንሽ አይናፋር፡ ሁልጊዜ ከእናቱ ቀሚስ ስር የማይለይ፡ ዙረታም፡ ሴታ ሴት ልጅ ነበር። በረከትን ለማግኘት፡ አሸንክታብ በላዩ ላይ አንጠልጥሎ፡ አባቱን አታለለ፤ ይሁን እንጂ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለሱ ተሰጥቶታል። አዎን፡ ተሰጥቷል።

185 ያኔ በዚያ ሄዶ-አማቹን-በዋሸው ጊዜም፡ ከኤርሞን በትር፣ ሽመልመሌ በትር ውሰዶ መንጋዎቹ ሲጸንሱ፡ ሽመልመሌ ከብቶችን ይወልዱለት ዘንድ፡ በውኃ ውስጥ አኖራቸው፡ በዚህም በማታለል ከብቶቹን የራሱ አደረጋቸው። እግዚአብሔርም ባረከው። ትክክል ነው።

186 ስለ ያዕቆብ ምንም የሚናገር ወዮለት። ታውቃላችሁ... በልዓም የተባለውን ሐሰተኛው ነብይ—ወይም፡ የተናገረውን ትክክል እንደሆነ ታውቂታላችሁ። እርሱም፡ አለ፦ “የሚመርቅህ ሁሉ የተመረቀ ይሁን፡ የሚረግምህም ሁሉ የተገመ ይሁን።”

187 “ያዕቆብ ሆይ፡ ወሰድኩህ። በእንግዳ ምድር እንደሚገኝ... አገኘሁት። ንሥር ጎጆዋን እንደምታነሳሳ፡ ቀስቅሼ ወሰድኩት።” ሃሌ ሉያ! “በመንፈሴ እንጂ፡ በኃይል፣ ወይም በብርታት አይደለም፣ ይላል ጌታ።”

188 ወደዚያ ፍጹምነት ሲወርድ ተመልከቱት። ያ መንፈስ በክርስቶስ እስከ ፍፁምነት ድረስ ሰራ፣ በእያንዳንዱ አባቶች በኩል፣ እስክ ታች ድረስ ወርዷል። ምንም ቢሉ፣ ምንም ቢሰሩ፣ ምንም ቢያደርጉ፣ ፍጹም የጻድቃን ዘር ነበሩ።

189 ክብር! እዚህ ጋር፡ ጻዲቁ፡ አብርሃም... ኦህ፡ ደስ ደስ አለኝ። ጻድቁ አብርሃም ራሱ እግዚአብሔርን መልከ ጼዴቅን በተገናኘው ጊዜ!

190 መልከ ጼዴቅ ማን ነበር? “የሳሌም ንጉሥ፣ እርሱም የኢየሩሳሌም ንጉሥ፣ የሰላም ንጉሥ ነው። አባት አልነበረውም። እናት አልነበረውም። ለሕይወቱም መጀመሪያ፣ ወይም ፍጻሜ የለውም።” ምንም ይሁን፡ አሁንም ህያው ነው። “ተወልዶ አያውቅም። ፈጽሞም አይሞትም። አባት ይሁን እናት በፍጹም ኖሮት አያውቅም። ለህይወቱም ቀናት መጀመርያ፡ ወይም ፍጻሜ በፍጹም አልነበረውም።” ማን እንደነበረ ንገሩኝ። ዘለአለማዊው አምላክ ነው፤ ማን ብለን ነበር የምንጠራው...

191 ኦህ፡ ማን ነበር የምትሉት ረሳሁት። እርሱ፡ ቲዮፈኒ ነው። ልክ እንደ... ተረት አይደለም፡ ነገር ግን በግልጽ የሚገለጥ ነው። ልክ ወደ አብርሃም እንደ መጣው፡ እንደ መልአክ፡ ትንቢት እንደተናገረ፡ ለሣራም ከበስተጀርባው ሆና፡ ሰቀሻል ብሎ እንደነገራት፡ እንዲሁ ህያው ነው። ነገሩ፣ ተመሳሳይ ነገር ነው።

192 አሁንም እነሆ። መልከጼዴቅን ተገናኘው። እና በቅመ-... በቅድመ-አያቱ በአብርሃም፡ በጻድቁ ዘር ሆኖ፡ ለመልከጼዴቅ አሰራትን ከፈለ፤ እዚህም ለቅመ የልጅ-ልጁም፣ ለጻድቃን ዘር ተሰጠ።

193 አሁን እዚህጋር ደግሞ የእ—የእባቡ ዘር መጣ። አሁን፡ በመካከላቸው፡ የጠላትነት ጦርነት፡ እንደሚሆን አስታውሱ።

194 የእባቡ ዘር ሲመጣ ማንን ወለደ? አሁን የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ዓመታት እንውሰድ። ምን እንደተፈጠረ አሁን ተከታተሉ። አሁን አረጋግጬዋለሁና፡ እስከ ታች ድረስ እናነበዋለን። የእባቡ ዘር ቃየንን ወለደ። ቃየን ወደ ኖድ ምድር ሄደና፣ ግዙፎችን ወለደ፣ ከዚያም ወደ ኖህ ምድር መጡ።

195 ብልህ፣ የተማሩ፣ እና አስተዋይ ሰዎች ነበሩ። ልክ ነው? ግንበኞች፣ ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶች ነበሩ፤ ይህም በእባቡ በሰይጣን ዘር ነው እንጂ፡ በጻድቃን ዘር አይደለም። እንደ—ሳይንቲስቶች፡ ግንበኞች፡ እና ታላላቅ ሰዎች፡ አስተማሪዎች፡ የመሳሰሉ ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። ናስን የሚሰሩ። የብረት ሰራተኞች። የተለያዩ ብረቶች ሰራተኞች ናቸው። ነገሮችን ፈለሰፉ። የተለያዩ ብረቶችን አቅላጮች፣ ቤቶችን ይሚሰሩ፣ ወዘተ። ይላቸዋል መጽሐፍ ቅዱስ። እንዲሁም በሴቲቱ ዘር፡ በጻዲቁ በኖህ ላይ ይሳለቁ ነበር። ልክ ነው?

196 ትንሽ ጠለቅ ብለን እንከተላቸው። ከዚያም ወደ መርከብ እናወጣቸዋለን፡ ሁሉም ነገር ወደመ። እንዲህ ባለው የኃጢአት ነገር ውስጥ ገቡ፡ በጣም ብልሆች እና ብልጦች ስለነበሩ፡ የመሪነቱን ሚና ወሰዱት። እግዚአብሔርም እስኪመለከታቸው፡ ድረስ፡ የቀረ አልነበረምና፡ ኖህን እና ቤተሰቡን ብቻ ወደ መርከቡ አስገባቸው፡ ዝናብን አዝንቦ ሁሉንም አጠፋቸው። ሄኖክን ግን፡

አስቀድሞ ወስዶታል። ልክ ነው? ሁሉም ዘር ማለት ይቻላል፡ ዘር የሆነ ሁሉ ነበረ፤ ነገር ግን ሊፈጽመው የፈለገ ዓላማ ነበረው።

197 አሁን ኖህ እና በሐረጉ የተቆጠሩ ልጆቹ፡ ሴም፣ ካም፣ እና ያፌት የጻድቃን ዘር ወገን ናቸው።

198 ታዲያ ዘሩ እንዴት ሊያልፍ ቻለ? ዘሩ ልክ እንደ መጀመሪያው፡ በሴቷ፡ በሚስቶቻቸው አማካኝነት፡ በመርከቧ ውስጥ ገባ። ቃየን በሴቲቱ በኩል ይወለድ ዘንድ፡ በሔዋን የሰይጣንን ዘር እንደያዘች፡ እነሱም በመርከብ ውስጥ፡ የሰይጣንን ዘር፡ ተሸክመው ነበር።

199 ሰባኪዎች አድርጋችሁ ሴቶችን በየመድረኮቻችሁ አውጥታችኋልን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ያወግዘዋል! ጳውሎስም አለ፦ "ማንም፡ ነቢይ ወይም መንፈሣዊ የሆነ ቢመስለው፡ ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ፤ ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን፡ አይወቅ።"

200 ከባፕቲስት ቤተክርስትያን ወደዚህ የወጣሁት በዚህ ምክንያት ነው። ወንድም ፍሊማን ቀደም ብሎ እዚህ ነበር፡ በዚያን ምሽት እርሱም እዛ የነበረ ይመስለኛል። ዶክተር ዴቪስ መጣና "ተነሰና እነኚህን ሴቶች ሰባኪዎች እንዲሆኑ ሹማቸው፡" አለኝ።

እኔም "አላደርገውም። በፍጹም፡ አላደርገውም፡" አልኩት።

እሱም "እንዲህ'ማ ከሆነ፡ አንተን አባርርሃለሁ፡" አለኝ።

201 እኔም "ከተሻለውም ተጥያለሁ፡" አልኩት እኔም፦ "ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ነገሩንም ያወግዛል። እግዚአብሔር ያወገዘውን ነገር ማድረግ አልችልም።" ኖ፡ ሰር።

202 ይህን የሚያደርጉ ሁሉ ግን፡ ሐሰተኛ አስተማሪዎች፡ ሐሰተኛ ነቢያት መሆናቸውን ያሳያሉ። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ ይላልና። "ቢቻል ኖሮ የተመረጡትን እስኪያስቱ።" ይሄው ነው።

203 አሁን ተከታተሉኝ። ከዛ በኋላ፡ ከመካከላቸው፡ ካም ወጣ። ካም እና ሚስቱ፡ ወጡ። እርሱም ተረገመ። ከካምም ባቢሎንን የሠራ ናምሩድ ተወለደ። የካቶሊክ ቤተ ክርሰቲያን፡ አጀማመርዋ ከባቢሎን ናት። ከዚያም አክአብ መጣ። ከአክአብ ቀጥሎ፡ የክርሰቶስ ተቃዋሚው፡ ያቆሰለው፡ የአሰቆርቱ ይሁዳ መጣ።

204 በዚህ ዘመንም፡ የክርሰቶሰ ተቃዋሚ መንፈሰ እና የክርሰቶሰ መንፈሰ ተፋጠዋል። የክርሰቶሰ ተቃዋሚው መንፈሰ፡ "የተአምራት ዘመን አልፏል፡" ይላል። የክርሰቶሰ መንፈሰ ግን፡ "እርሱ ትናንትናም፣ ዛሬም፣ ለዘላለምም ያው ነው፡" እያለ ነው። የክርሰቶሰ ተቃዋሚ መንፈሰ ይላል፦ "'በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈሰ ቅዱሰ' ወይም በሌላ ብትጠመቅ፣ በመረጨትም ይሁን፣ ውኃን በማፍሰሰ፣ ምንም ይሁን፣ ያው ነው።" መጽሐፍ ቅዱሰ ግን እግዚአብሔር አይሳሳትም፣ አይለዋወጥም ይላል። የምታገለግሉት ማንን ነው? እንደፈለጋችሁ።

205 አሁን እናንተ፦ "አብረው ይሆናሉን? ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አንተ ስትናገር፡ በመርከቡ ውስጥ፡ ካም እና ሴት አብረው ነበሩ፡ ብለሃል።" አዎን

እውነት ነው፡ ትክክል ነው። ካም ክፉ ሰው ነበር። ሴት ግን ጻዲቅ እና መንፈሳዊ ነበር። በጣም ጥሩ።

206 ካምን እንከተል። በጣም ጥሩ፡ አሁን፡ በአንድ መርከብ ውስጥ፡ ካም እና ሴት፡ ጻዲቁ እና ሐጢአተኛው ነበሩ። በአንድ መርከብ ውስጥ ቁራ እና ርግብ ነበሩ። በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይሁዳ እና ኢየሱስ ነበሩ። በዚያው ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ተቃዋሚና መንፈስ ቅዱስ ነበሩ።

207 ዛሬም፡ ያንኑ መንፈስ፡ ስራ ላይ ነው። "የአምልኮት መልክ አለው፣ እጅግ ሃይማኖተኛ፣ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉንም ግን ክደዋል፤ ከእንዲህ ዓይነቱ ራቅ።" መንፈስ ቅዱስ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፣ ዛሬም፣ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡" ብሏል። የትኛውን ወገን ትመርጣላችሁ?

208 የክርስቶስ ተቃዋሚው **ይህ** የእምነት መግለጫ መጽሐፍ ብቻ ነው ይላል። "የሐዋርያትን የእምነት መግለጫ እንደግማለን።" የሐዋርያት የእምነት መግለጫ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚገኝ ማሳየት የሚችል ሰባኪ ይምጣ እወራረዳለሁ፤ "በእግዚአብሔር፣ ሁሉን በሚችል አባት፣ የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ በሆነው፡ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አምናለሁ። በቅድሰት ሮማዊት ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፣ በጻድቃናት ተራዳኢነት አምናለሁ።" መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን ከየት አገኛችሁት? አሁንም በሜቶዲስት እና በባፕቲስት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ትደግሙታላችሁ። የዲያብሎስ ትምህርት ነው፡ ሐሰተኛ ነቢያትም እያስተማሩት ነው።

209 ስሜታችሁን እንዳልጎዳኋችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ፡ እኔ ግን ይህ ሁሉ ለዚህ ህብረት እላለሁ። በብራንሃም ተበርናክል ያላችሁ ሰዎች፡ ከእነኚህ ዓይነት ነገሮች ራቁ። በጻድቃን ተራዳኢነት የሚያምን ማንኛውም ነገር መናፍስታዊነት ነው። "በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።" ምንም ያህል ማርያሞች ቢኖሩ አይገደኝም!

210 ያኔ የሴቷ ዘር በዚያ ያደረገውን ነገር አይታችኋል? የሴቲቱ ዘር በዚያ የፈጸመውን ነገር አይታችኋል?

211 ዛሬ አሜሪካ ውስጥ፡ ተመልከቱ። አሜሪካ የዲያብሎስ ዘር ነች። በምን ምክንያት? የሴት ሀገር ነች። "ይህች የሴት ዓለም ናት፡" ሲባል ሰምታችኋል። አዎን። የሴት አገር ነች። ስርዓትም አበጅተውለታል።

212 ቅርብ ጊዜ፡ አንድ ቦታ ሄጄ ነበር፡ ወደ ሰዊዘርላንድ። ሴቶቹ ሲናገሩ... መንፈስ ቅዱስ የተሞላች፡ አንድ ምስኪን ሴት "ታውቃለህ፡ እኔ አሜሪካ ብሄድ፡ ሴቶች ነጻነት አላቸው ይባላል፡" አለችኝ።

213 እኔም "ወዴት እንደሚመራሽ እኔ እነግርሻለሁ፡" አልኳት። እና መናገር ጀመርኩ።

አሷም "እቤቱ፡ ማረን፡ እንዲህ'ማ ከሆነ እንዳቸውም አልፈልግም፡" አለች።

እኔም "ወደዚያው ይመራሻል፡" አልኳት።

ታውቃላችሁ፡ እዚህ እንደምታደርጉት ነገር እዛ አያደርጉም።

214 ምንድን ነው? አሜሪካ ሴት መሆኗን እስቲ ላሳያችሁ። እዚህ ያለው ሁሉ ስለ ሴት ነው። በሳንቲማችን ላይ የሴት ምስል አለበት።

215 ንገሩኝ እስቲ፡ በዚህ አገር ውስጥ ብዙ ሕገ ወጥ መጠጥ ቤቶች ባይኖሩ፡ በዚህች ከተማ... አርባ ያህል ህገ ወጥ መጠጥ ቤቶች አድርጉና፡ በጎዳናው ላይ ደግሞ እጅግ-የሚያማምሩ ሰውነታቸውን የሚያውረገርጉ፡ ሶስት ሴተኛ አዳሪዎችን አቁሙ፤ የከተማው መጠጥ ቤቶች ወደ ሲኦል ከሚልኳቸው ነፍሳት ይልቅ፡ እነሱን አይተው በመመኘት ወደ ሲኦል የሚወርዱ ነፍሳትን ይበዛሉ። በትክክል እውነት ነው።

216 እንግዲያውስ ማን ናት? ሴት ናት። እሷ ምንድን ናት? የአሜሪካ አምላክ ነች።

217 ከድሮ የፊልም ተዋናዮች መካከል አንዳንዶቹን እናንሳ፡ እየተነሱ አራት አምስት ጊዜ ያገባሉ፡ በአንድ ጊዜ ከሶስት ከአራት የተለያዩ ባሎች ይኖራሉ፤ አንዳንድ መጽሔቶችም እርቃናቸውን የሚያሳይ ፎቶግራፍ በማንሳት፡ ያጋልጧቸዋል ይናገሩላቸዋል። እናንተም ልጃገረዶች ምሳሌዎቻችሁ ታደርጓቸዋላችሁ፡ (ለምን? ) ምክንያቱ እናትሽ፡ ኧረ ምናልባትም፡ አያትሽ ካንቺ በፊትሽ አለች። የእባቡ ዘር የት እንደሚሰራ አያችሁ? በእርግጥ፡ እንዲህ ነው።

218 እና ምን ይደረጋል? በሕጉ መሠረት፡ ኃጢአት እስከ አሥራ አራት ትውልድ ድረስ ከመጣ፡ በዚህ በጻድቃን ዘር መጨረሻ ዘመን ኃጢአት የት ድረስ ይደርስ ይሆን? እግዚአብሔርም የሚመጣ ጊዜ አለ፡ ያንን ጊዜ ግን እርሱ ባያሳጥረው፡ አንድም ሰው ባልቀረ ነበር በማለት ተናግሯል። እኛ በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነን። ወደየ ከተሞቹ ዙሩ፤ ዛሬ ጻዲቁን አድኑ!

219 ኦህ፡ የቤተ ክርስቲያኑ አባላት፡ የተቻላቸውን ያህል፡ ለባፕቲስቶች እና ለፕሪስባይቴሪያን ታማኝ ሆነው ታገኟላችሁ። ከእግዚአብሔር ጋር ግን ጥንቸል የበረዶ ጫማ ከማጥለቅ የዘለለ ጉዳይ የላቸውም። ምንም አያውቁም! የሚያውቁት ነገር፤ "ክርስትያን ነህ? "

"ካቶሊክ ነኝ።"

"ክርስቲያን ነህ? "

"ባፕቲስት ነኝ።"

"ክርስቲያን ነህ? "

"እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ።"

"ክርስቲያን ነህ? "

"እኔ ጴንጤ ነኝ።" ይህ ከሱ ጋር ምንም አይገናኝም።

220 እግዚአብሔር፡ በጸጋው ስላዳነህ፡ ክርስትያን ሆነኃል። እንዲህ እንደሆነም ታውቃለህ። ይሁን እንጂ ሌላ ኑሮ ትኖር ዘንድ፡ የቀየረህ አንድ ነገር አለ። እናንተ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ሰው እና አዲስ ፍጥረት ናችሁ። በትክክል።

221 ነገር ግን የእባቡ ዘር የት ነው? የእባቡ ዘር ምን ነበር? ዝሙት። እየተከታተላችሁ ነው? ከሔዋን ጋር ዝሙት ሰራ። ይሄስ ምን አመጣ? መዘዙ ምን ነበር? ዛሬ ማታስ ምንድነው?

222 ወደ ኋላ ተመልከቱ፣ ከጥቂት አመታት በፊት፣ የመጀመሪያዋ ዘፈን ስትወጣ። እናንተ የእድሜ ባለጸጎች፡ ያኔ ድሮ... ዘፈኖች ሬድዮ ላይ ከመተላለፋቸው በፊት ሳንሱር ይደረጉ ነበር። እና መጀመርያ የተለቀቀች ዘፈን፡ እንዲህ ነበረች፡ "ሴቶች ሆይ፡ ከፍ ክፍ አርጉት፣ ጉልበታችሁን አሳዩ፡ ከፍ ከፍ አርጉት፣" እንዲህ የመሳሰለ ነበረ። "ባባ እና ማማ ላይ ሳቂባቸው፡ አብዝተሽ 'ሃ-ሃ-ሃ!' በያቸው" መጀመርያ የተንሸራተቱባት እቺ ነበረች። ያንን ዘፈን የጻፈው ሰውዬ ዛሬ ማታ የት ነው ብላችሁ ታሰባላችሁ? ሞቷል።

223 መጀመሪያ ወጥታ፡ **አደገኛ ኩርባዎችን**፡ብላ የተናገረች ሺዎች ነፍሳትን ወደ ገሃነም የላከች፡ ክላራ ቦው የተባለች ያቺ ራቁት ዳንሰኛ ሴት የት ናት ብላችሁ ታሰባላችሁ? ዛሬ ማታ የት ናት ትላላችሁ? ከሞተች ብዙ ጊዜ ሆኗታል። ያንን አካሏን ይዛ፡ በዚህ ሰዓት የት ናት? ጉድጓድ ውስጥ፡ በአፈር ተወራለች፡ ትሎች እና ትላትሎች በልተዋታል። ነፍሷም በጻድቅ አምላክ ፊት ወድቋል።

224 ያቺን ሴት ወሰዶ አሁን የሚለብሱትን የማይሆናቸው ክፉ-ልብሰ ያዘጋጀላቸው፡ ገሚሱ በዚህ በኩል ሌላውም በዚያ በኩል እንዲሆን፡ ያሰደረጋቸው ሰው የት አለ? እሰቲ፦ "ለምን እንዲህ ያደርጋሉ? እነኚህን አይነት አልባሳት ለምን ትለብሳላችሁ? " ወንዶች እንዲያዩአችሁ ሰለምትፈልጉ፡ ሌላ ምክንያት የለውም።

225 ታውቃላችሁ እንዲህ ለብሳችሁ፡ አንድ ሐጢአተኛ ሰው ሲያያችሁ፡ ምን እንደሚፈጠር ታውቃላችሁ? በፍርድ ወንበር ፊት... እናንተ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኔ ለባሌ እስከ መጨረሻ ድረስ ታማኝ ነኝ፡" ትላላችሁ። እናንተ ግን ዝሙትን በመፈጸም ጥፋተኛ ትቆጠራላችሁ። ኢየሱስም "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሰዋ ጋር አመንዝሮአል፡" አለ። ያ ሰው ስለ ዝሙት በመፈጸሙ ምክንያት ሲጠየቅ፣ ይህን ያደረገው ማን ሊሆን ነው? ለብሰሽ እራሰሽን ያሳየሽበት መንገድ ነው።

226 አሁን፡ ከጥንት ሣጥን እንደወጣች እንደ ሌላ ነገር መልበሰ አለባችሁ ማለቴ አይደለም። ነገር ግን፡ እመቤት መምሰል ትችላላችሁ።

227 አጫጭር ልብሶቻችሁን ለብሳችሁ፡ ትንሽ ሪባን ጣል አርጋችሁበት፡ **እንዲህ** ትወጣላችሁ፡ የልጆቻችሁ ዓይኖች እንደ ሲጋራ ትሬ፡ ሲጋራ አፋችሁ ውስጥ ሰክታችሁ፡ ሰፈር ለሰፈር ትዞራላችሁ። ያለ ምንም ምክንያት አታደርጉትም። በነገሩ ላይ ንጹህ ሰዎች ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ ዲያብሎሰ ግን ሔዋንን እንደተጠቀመባት እንደመሳርያ ይጠቀምባችኋል።

228 ለምን የሴት አገር ሆነች? ምክንያቱም ወደ ካቶሊካዊ የበላይነት እያደገች ሰለሆነ። ዛሬሰ ምንድን ነው? ኢየሱሰ ብለው ሰሙን ሲጠቅሱ ፈጽማችሁ አትሰሟቸውም። "ሰላም ለኪ ማርያም! ማርያም የእግዚአብሔር እናት ሆይ! ቅድሰት ሴሲሊያ!" ሁሉም ዓይነት ቅዱሳን፣ የሞቱ ጻድቃን። በቅርብ ጊዜ ነው፡ በ...

229 አምና፡ ሜክሲኮ ነበርኩ። አንዲት ምሰኪን ሴት፡ እየጎተተች መጣች። ጉልበቷ ሁሉ፡ እንዲህ በንብርክክ፡ ተሸፋፍና፡ እያለቀሰች፡ እጆቿን አጣምራለች። አባትዬው ሁለት ህጻናት ልጆች ይዞ፡ እያዘገመ ይሄዳል፡ እናታቸው ክፉኛ ትሰቃያለች፡ ልጆቹ ያለቅሳሉ፡ ምክንያቱ፡ ቅድሰት ብለው የሚያምኑባት አንዲት

ሴት፡ ሰለሞተች። ተራራው ራስ ላይ ሐውልት አሰርተውላታል። አፍቃሪዋ ነበር የገደላት። ልክ እንደተገደለች፡ እርግጥ፡ ቅድስት ነች፡ ካቶሊክ ናትና። ስለዚህ ንስሐ ልትገባ እየሄደች ነበር፡ ንስሃ ለመግባት በኮብልስቶን ላይ ሁለት ማይል ርቀት በንብርክክ መሄድ ነበረባት።

230 ወንድሜ፡ እኔ የማደርገው አንድ ነገር ካለ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከንቱ ሞተ። በጸጋ፡ ድኛለሁ፤ በኔ አይደለም—በኔ ሳይሆን፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ፡ እና በእግዚአብሔር በጎነት ነው።

231 እነኚያ ጋዜጠኞች፡ ጠየቁኝ፡ "ሚስተር ብራንሃም... " የሞተው ህ—ህጻን ልጅ፡ ወደ ህይወት ተመለሰ፡ ሌላ ጥቂት ነገሮችም ሆነዋል። ሠላሳ ሺህ ካቶሊኮች... አይ፡ ይቅርታ። ሃያ ሺህ ናቸው። ሰላሳ ሺህ የአፍሪካው ነው። ሀያ ሺ ካቶሊኮች ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ አድርገው፡ በአንድ ጊዜ ተቀበሉ፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ፡ በሜክሲኮ ሲቲ ነበርን። እና ቄሶቹ፡ ምንም ማለት አልቻሉም፡ በጣም ብዙ ናቸው፡ ግርግር ጀመሩ። ጎን ላይ በጣም ብዙ ነበሩ። እና እንዲህ አሉኝ፦ "ሚስተር፡ ብራንሃም፡ አንተ የምታደርገውን ተመሳሳይ ነገር ቅዱሳኖቻችን ያደርጋሉ ብለህ ታምናለህ? "

232 ዶክትሪናቸው ሰለማውቀው፦ "አዎን፡ ህያዋን ከሆኑ ይችላሉ፡" አልኳቸው። እያችሁ? እና አንድ ሰው ካልሞተ፡ በካቶሊክ ቅዱስ መባል አይቻልም፡ ይሄን ታውቃላችሁ።

እሱም "ኦህ፡ እሰክትሞት ድረስ'ኮ ቅዱስ መሆን አይቻልም፡" አለ።

233 እኔም አልኩት፦ "ከየት ነው ያነበብከው? " ጳውሎስ ሲናገር፦ 'በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን፡' በእግዚአብሔርም ለተጠሩ ብሏል። 'በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን፡' መልእክቱን ያነብ ነበር፤ እንዲሁም በየሰፍራው ላሉ ቅዱሳን፡ በገላትያ፣ እና—እና 'በሮም ላሉ ቅዱሳን፡' ወዘተረፈ። **ቅዱሳን** ለሆኑት፡ 'ለተቀደሱት።' ይሄኛውስ? "

234 እሱም አለ፦ "እርግጥ፡ አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ አያከራክረንም። ምክንያቱ፡ ቤተ ክርስትያን ይሁን ለምትለው ሁሉ፡ ቤተ ክርስትያን ነንና። ቤተ ክርስትያን ይሁን ለምትለው እንጂ። መጽሐፍ ቅዱስ ለሚለው ግድ የለንም።" "ስለ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስትያንስ ምን ታሰባለህ? " አለኝ፤

235 እኔም "ይሄን ጥያቄ ባትጠይቀኝ ጥሩ ነበር። ስለጠየቅከኝ ግን፡ እውነቱን እነግርሃለሁ፡" አልኩት።

"እሺ፡ እውነቱን እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ፡" አለኝ።

"እሉ ከሚባሉ ከፍተኛ አጋንንታውያን አይነት ናት፡" አልኩት።

"እንዴት እንዲህ አልክ? " አለኝ፡

236 "ሙታንን እንደ አማላጅ የሚጠቀም ሁሉ አጋንንታዊ ነው፡" አልኩት። "ያ ቅዱስ የተባለው ከመለሰ፡ ሲኦል ውስጥ ነው ማለት ነው። ምክንያቱ፡ መጽሐፍ—ቅዱሴ እንዳለው፡ አድማስን ተሻግሮ የሄደ አይመለስም ይላልና።" ትክክል ነው። "በመጀመርያ ደረጃ፡ ከተሻገረ፡ ቅዱስ ከነበረም፡ ቅዱሳንን በማሰመሰል የተናገረው ዲያብሎስ እንጂ፡ ቅዱሱ አይደለም፡" አልኩት።

237 እሱም "እሺ፡ አሁን፡ ቆይ አንድ ደቂቃ።" "አንተም'ኮ፡ ሙታንን ማልደሃል፡" አለኝ።

“የት? ” አልኩት፤

“ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቷል፡” አለኝ።

238 እኔም፦ “እሱ እንደገና ተነስቷል። ሙታን አይደለም። እርሱ ግን፡ ሊያማልድ በሕይወት ይኖራል፡ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለ ብቸኛ አስታራቂ እሱ ነው።”

239 “ሞቼ ነበርኩ፤ አሁን ግን ሕያው ሆኜ እስከ ዘላለም ድረስ እኖራለሁ። የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ።” “የተጠማ ቢኖር፡ መጥቶ ከሕይወት ውኃ በነጻ ይጠጣ።” ማይ! አምላካችን ይህ ነው። አምላካችን ይህ ነው።

240 አሁን የጻድቃንም ዘር እያለቀ ነው። ስለእነዚህ ነገሮች ከሰዎች ጋር ተናገሩ። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መንገድ ስለመመለስ ከሰዎች ጋር ተናገሩ። ስለ ተአምራት ለሰዎች ተናገሩ። ስለዚህ ጉዳይ ከህዝቡ ጋር ተናገሩ። ሁሉም “ቤተ ክርስቲያናቸው አታምነውም፡” ስለዚህ ለእግዚአብሔር፡ ሁሉም ዲቃላ ልጆች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰደትን፣ ፈተናን፣ ፌዝን፣ እና “ሆሊ-ሮለሮች” እና የመሳሰሉትን፣ መሸከም ካልቻልን እንዲህ ይላል፣ ይህ መቋቋም ካልቻላችሁ፣ እናንተ ዲቃላ ልጆች እንጂ የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም። መጽሐፍ ቅዱስም ይላል።

241 ብትፈልጉ “ሆሊ-ሮለር፡” በሉኝ። የፈለጋችሁትን ጥሩኝ። ልቤ በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክል እስከሆነ ድረስ፣ ልምምዴም ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ እስከተሰማማ ድረስ፣ በአንዱ አቅጣጫ በቀጥታ እየተጓዝኩ ነኝ። የሰ፡ ሰር። እኛ የምናምነው ይህ ነው። በሥነመለኮት ያልመጣች፡ የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ይህች ናት። በአንዳንድ ሰው-ሰራሽ፣ ምሁራዊ ፅንስ ሀሳብ አልመጣችም። የመጣችው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በተገለጠው ፍጹም እውነት ነው።

242 የባፕቲስት ወይም የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን፣ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ብለው ስላስተማሩኝ ብቻ ምሁራዊ ፅንስ ሀሳብ ብቻ ቢኖረኝ፣ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ ሰሰማ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከሆነ... ይህን መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤ “በአባት፣ ልጅ፣ መንፈስ ቅዱስ፡” ስም የተጠመቀ ሰው ብሆን፡ እና አንድ ሰባኪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በቀር በሌላ ስም የተጠመቀ ማንም እንደሌለ ቢነግረኝ፣ እኔም አንብቤው እውነት እንደሆነ ካየሁ፡ በተቻለኝ ፍጥነት ውሃው ውስጥ እገባለሁ። የሰ፡ ሰር።

243 ፈውስ የሚፈልግ ሰው ስለሆንኩ አንድ ሰው—ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ፈዋሽ እንደሆነ ቢነግረኝ፣ ቤተ ክርስቲያኔ ግን፡ “የተአምራቱ ቀናት አልፈዋል፣” የምትል ከሆነች፣ በቻልኩት ፍጥነት ለፈውስ ወደ መሠዊያው እሮጣለሁ። እርግጠኛ ነኝ አደርገዋለሁ።

244 እኔ ሰባኪ ብሆን እና—አንዲት ሴት ሰባኪ ፑልቢቴ ላይ ካለች፣ እኔም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አንብቤ ሴት መሰበክ እንደሌለባት ከተረዳሁ፣ የጀርባዬ ቆዳ ቢገፈፍም፡ ከቦታው አሰወግዳታለሁ።

245 አንድ ቀን ማታ፡ እህት ራይት በተቀመጠችበት፡ ወደ ኋላ አካባቢ ነበርኩ፡ እንዲህ ሰላልኩ ብቻ በር ላይ ልትጥለኝ የሞከረችውን ሴት ታስታውሷታላችሁ። የሰ፡ ሰር። እኔ ያልኩት፡ “እንዲህ አይነት፡ አሽንክታብ

ሊብሳችሁ ወደ ቤተ ክርስትያኔ መምጣት… ” ያኔ የነበረው አለባበሳቸው፡ በዚህ በኩል እስከታች ድረስ ይቆርጡታል፣ ግማሽ ገላቸው እርቃን ይሆናል፡ ለማየት እጅግ-የሚቀፍ ነበር። “ወደ ቤተ ክርስትያኔ ቢመጡ፡ እርግጠኛ ነኝ አስወጣቸዋለሁ፡” አልሁ። እና አንድ ፍሪዝ-ጎፈሬ እዛ ጋር የነበረች፡ በኋላ’ኳ ብዙም ሳትቆይ ሞታለች፡ ሞት አፍ ላይ ሆና፡ ጠርታኛለች። የካቶሊክ ልጅ ናት፡ እና እንዲሁ ለባብሳ መጣችና ቁጭ አለች። ወደ ኋላ ተመለከትኩና፡ እዛ ጋር ተቀምጣ አየኋት፡ ሌሎቹ እየዘመሩ ነበር። ኮቴን አውልቅኩና፡ ወደሷ ሄጄ፡ ትከሻዋ ላይ አደረግኩላት። እኔም አልኳት፦ “እመቤት፡ እኔ ስሰብክ መስማት ከፈለግሽ፣ እባክሽ በእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን እስካለሽ ድረስ ይህን ኮት ልበሺ።” አያችሁ? ግድ ነው።

246 ፈነጠር ብላ ተነሳችና፡ ከንፈሮቿን ወደ ላይ ዘረጋቻቸው። ወድያው ከህንጻው ወጣች። ከዛ “ሐይማኖት አለኝ የሚል ከሆነ፣ እንዲህ አይነቱ ሐይማኖት ለላሜ’ኳ አልመኝላትም፡” ብላ ተናገረች።

እኔም “ግድ የለሽም፡ አይኖራትም፡” አልኳት።

247 ከዛ በኋላ የድንኳን ጉባኤ በነበረን ጊዜ፡ እየሞተች ነው ብለው ጠሩኝ። ድንገተኛ የልብ ህመም ደርሶባት፡ እየሞተች ነበር። ጉባኤ መካከል ነበርኩ። ባሏ መጣ። እሱም፡ “በፍጥነት ናልን!” ትልቅ፡ ረዘም ያለ ሰው፡ በሩ ላይ ቆሞ እየጠበቀኝ ነው። ፈጥቼ ወጣሁና…

248 መኪናዬ ውስጥ ገብቼ ሮጬ ደረስኩ። ወደ ላይ ሰወጣ፣ እስከ አሁን ድረስ፡ በሃዋርድ ፓርክ ውስጥ የምትኖረውን የቆየች ነርስ አገኘኋት። “ሬቨረንድ፡ መምጣት አያስፈልግህም ነበር፡” አለችኝ። የዛሬ ሀያ አመት በፊት ነው፡ ሊበልጥም ይችላል። እና “ሞታለች፡” አለችኝ። “ከሶስት ደቂቃ በፊት ሞተች፡” አለችኝ። “አንተን ለማግኘት የቻለችውን ያህል፡ ጮኻለች፡” አለችኝ። “መልእክት ትታልሃለች፡” አለችኝ።

“ምን? ” የሚል፤

249 “ያን ሰባኪ፡ ስለተናገርኩት ነገር፡ ‘እባክህ ይቅር በለኝ በሉት።’” ብላለች።

250 እሷን ለማየት ወረድኩ። ቆንጆ ሴት፡ እጅግ ተሠቃየች። በአፍንጫዋ ላይ ትንሽ ጠቃጠቆ ያለት፡ ቆንጆ ሴት። እና ጠቃጠቆዎቹ፣ ጎልተው የወጡ፡ ይመስላሉ። ዓይኖቿ ከዓይን ጉድጓድ ተገፍተው ወጥተው፡ በግማሽ ያህል ወደ ኋላ ተመልሰዋል። እርግጥ ነው፣ አንጀቷና ኩላሊቶቿ ተንቀሳቅሰዋል፣ እንፋሎቱም በአልጋው ላይ፡ እንዲህ ይወጣል።

251 ባሏም አየኝና፦ “ወንድም ብራንሃም፣ አንተን ለማየት ስለፈለገች፡ ጸልይ፡” አለኝ።

እኔም “አሁን ለእሷ ጸሎት ምንም አይጠቅምም፡” አልኩት።

252 አያችሁ? “ዛፍ ዘንበል ወዳለበት፡ ይወድቃል።” “አትሳቱ፡ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ያጭዳል።”

253 የት እንዳለ ታያላችሁን? አሁን ምን ተፈጠረ? እንዲህ መሆን የምትፈልግ ሴትን ተመልከቱ። ድሮ ከነበሩት ሴቶች መካከል፡ ተወዛዋዥ ሴት የነበሩትን ተመልከቷቸው፡ ልጇ ምን ነበረች? ተወዛዋዥ። የተወዛዋዥ ልጅ ምን

ትሆናለች? ሮክ-ኤንድ-ሮል ታዳጊ። የሷ ልጅስ ምን ትሆናለች? አይይ! ምንድናት?

የጻድቁን ዘር አያችሁት?

254 ባፕቲስቶች ሆይ ራሳችሁን ተመልከቱ። ጥቂት ወደ ኋላ ተመለሱ። ባብቲስቶች ሆይ፡ መስራቻችሁ ወደ ሆነው፡ ጆን ስሚዝ መለስ ብላችሁ እዩ። ዓይኖቹ አብጠው እስኪደፈኑ ድረስ፡ ሚስቱም ጠረጴዛው ላይ፡ ቁርሱን እስክታበላው ድረስ፡ ስለ ሕዝብ ሁሉ ይጸልያል፡ ስለ ሕዝቡ በደል፡ ያለቅሳል ይጸልያል።

255 እናንተ እዚህ ያላችሁ፡ አፍንጫችሁ ላይ፡ እና ጆሮአችሁ ላይ ጌጥ ያለባችሁ ሜቶዲስቶች ሆይ፡ የዲያብሎስ የጎን መጫኛ መስላችሁ፡ አጫጭር ልብሶች፡ እና አሸንክታቦች ለብሳችሁ፡ ትወጣላችሁ! ከሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች አንዱ የነበረው ጆን ስሚዝ ግን፡ ከመሞቱ በፊት፣ በሰማኒያ-አምስት ዓመቱ፣ አራት ዓመት፡ ማለቴ፡ የአራት ሰዓት አጭር ስብከት ይሰብካል። ተሸክመውም ቍልቢት ላይ ያወጡት ነበር። እና የመጨረሻ ቃላቶቹ እነዚህ ነበሩ። እርሱም "እኔ በሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ድርጊት በጣም ደንግጫለሁ፡" አለ። "የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ሴት ልጆች ሳይቀሩ ጣታቸው ላይ የወርቅ ቀለበት ለብሰዋል፡" ብሎ ተናገረ። ታድያ አሁን፡ ቁምጣ ለብሰው፡ ኳየር ላይ የሚዘምሩትን ቢያይ ምን ይላል?

256 መልካም ተጉዛችሁ ነበር። አሁን ምን ገጠማችሁ? የእናታችሁ ዓይነት ተግባር ጀመራችሁ። ትክክል ነው።

257 እነኚህ የሀይማኖት ተቋማት፡ በዚህ ዙርያ ላይ ተንጠልጥለው፡ እዚህጋ፡ ተጣብቀው፤ "እኛ ሜቶዲስቶች ነን። እኛ ባፕቲስቶች ነን።" የክርስቶስ ብቻ ነን። ተዉት፡ ነፃ ሁኑ።

258 እሺ፡ የእባቡን ዘር አያችሁት? እንዲት የወጣች ሴት ምን ትፈልጋለች? ምን ታደርጋለች? ምን? ደግመው ደጋግመው፡ እየወጡ ነበር። ከዛ ባፕቲስቶችን ወደ ኋላ መለሱ፣ ሜቶዲስቶችን ወደ ኋላ መለሱ፣ ፕሬስባይቴሪያንን ወደ ኋላ መለሱ። ለምን ተመለሱ? ሁሉም ወደ አሮጉቷ፡ ወደ እናታቸው፡ ወደ አመንዝራዋ ተመለሱ። በዚያም ሁሉም፡ አንድ አይነት ዝሙት እየሰሩ ነው። "በቃ፡ በጥልቅ ውሃ ውስጥ ቢገቡ። ወይም በውኃ ቢረጩ። ጥሩ አባላት ቢያመጡ። እነሱም፡ ጥሩ ከፋዮች፡ ቢሆኑ። የስድስት ወር ክልከላቸዉን ተቀብለው፡ በዚያ ጊዜ ውስጥ ብዙ ባይጠጡም፡ ወዘተረፈ። መጥተው ቢናዘዙ። ልዩነት አይፈጥርም… " ኦህ፡ ማይ! ያ ከመንፈስ ፍሬዎች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም።

259 የመንፈስ ፍሬዎች "እምነት፣" ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና፣ ዛሬ፣ እስከ ለዘላለምም ያው መሆኑ ማመን፣ "ፍቅር" ለወንድሞች፣ "ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ በጎነት፣ ገርነት፣ ትዕግሥት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት።" እንዲህ ነው ነገሩ፡ የመንፈስ ፍሬ ይህ ነው።

260 እናም አንድ ሰው እንውሰድ፦ "እንግዲህ፡ ሰውየው በሰፈር—በመንደሩ ጥሩ ኑሮ ይኖራል።" ኤሳውም ያው ነበር።

261 ዔሳው የዲያብሎስ ነበር፤ ዔሳው ግን አንድም ሰው ጎድቶ አያውቅም፡ ያዕቆብ ግን፡ከአንድ ማህጸን የወጣ፡ የእግዚአብሔር ነበር። የዲያብሎስ ዘር፤ የሴቲቱ ዘር፣ የእግዚአብሔር ዘር ይቀጥላል።

262 አሁን፡ ሁሉም ዛሬ በዓለም ላይ ወደ ቀረው፡ ወደዚህ፡ መድረሳቸውን አይታችኋል? ይህንን በእውነት አምርሬ እናገራለሁ፡ ከፈጸምኩ በኋላ፡ ከዛ በኋላ በሚቀጥለው ስብሰባ ላይ፡ ሪቫይቫል እንጀምራለን። ቅርጽ ይዟል። እና፡ እባካችሁ፡ እኔ ይሄን ስናገር ለመመናፈስ አይደለም። ክፉ ለመናገር አይደለም። ወደ አንድ ትልቅ፡ ሕገ ወጥ ሐይማኖታውያን ልጆች፡ ወደ ዲቃላ ልጅነት፡ ደርሰዋል። የመጨረሻ አስተያየቴ ይህ ነው። ወደ እንደዚህ አይነት በትክክል ደርሰዋል። እውነት እንደሆነ እናንተም ታውቃላችሁ። "የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል፡" ቸርች-መቀላቀል እና የቸርች-አባል ወደ መሆን፣ የሐይማኖት ኮተት፡ የዲቃላ ልጆች እስከ መሆን ድረስ ወርደዋል። እውነቱ ይህ ነው።

263 ቀጥሎ ምን ይቀራል? ብዙ፡ የተንጠለጠሉ ሮኬቶች፣ የኮባልት ቦምቦች እና ሌሎች ነገሮች። ያቺ ሰዓት እስክትመጣ ድረስ እየጠበቁ ናቸው። በውኃም እንደነበረ ጥፋት፡ በእሳት ጥፋት ይሆናል።

264 ወዳጆች ሆይ፡ ምንም ብታደርጉ፡ ክርስትያኖች ከሆናችሁ፡ እግዚአብሄር በልባችሁ ውስጥ ካለ፡ ከሞት ወደ ህይወት እንደተሻገራችሁ ካመናችሁ፡ በዓለም ሁሉ ካሉ ሰዎች ይልቅ ደስተኞች መሆን አለባችሁ።

265 መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥ ሲኖር... መጽሐፍ ቅዱስ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ዛሬም እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡" ሲል፤ የሐይማኖት ተቋማት "እኛ ግን የተአምራት ዘመን እንዳለፈ እናምናለን" ሲሉ፤ መንፈስ ቅዱስ፡- "አሜን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፣ እስከ ለዘላለምም ድረስ ያው ነው ይላል። አሜን።"

266 መጽሃፍ ቅዱስ ይላል፡- "ንስሐ ግቡ፡ ሐጥያታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ መንፈስ ቅዱስም ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተ፣ ለልጆቻችሁ፣ ለአሕዛብ፣ ጌታ ከአምላካችን ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና... " (ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው ሁሉ፡ እያችሁ፡ ሜቶዲስት ለሚጠራቸው ሁሉ፣ ባፕቲስት ለሚጠራቸው ሁሉ ሳይሆን፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው ሁሉ፡ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጠመቃሉ፡ ይላል መጽሀፍ ቅዱስ)፤ ይህ ሲነካችሁ፡ "አሜን!" ትላላችሁ፤

267 ቤተ ክርስቲያን ግን "ያው ነው፡ ልዩነት የለውም፡" ትላለች።

268 በእናንተ ውስጥ ያለው መንፈስ ቅዱስ ግን ለቃሉ "አሜን" ይላል።

269 "ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።" ይኸው ነው።

270 እየተፈጸመ ያለው ነገር ሁሉ እንዲሆን ያስቻለው አፐል ነው የሚል አንድ ቃል እንድታሳዩኝ እወራረዳለሁ። አፐል መብላታቸውን እንድታሳዩኝ እፈልጋለሁ። ቃየን ያሰበው ተመሳሳይ ነገር፡ ዘሩም እስከ አሁን ድረስ አንድ አይነት ነገር እንደሚያስብ አሳይቻችኋለሁ።

271 በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠው፡ የእግዚአብሔር መንፈሳዊ መገለጥ ግን፡ በወንድና በሴት መካከል የተደረገ፡ ሕገ ወጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንደነበረ ያስረዳል። ግዙፎች የመጡበት ሁኔታ ይህ ነው። ኃጢአታችሁ የመጣው ከዚህ ነው። እርኩሰት ሁሉ የመጣው ከዚህ ነው። የወረደው ከዚህ ነው።

272 አሁን ይህን አስተውሉ—ተመልከቱ፡ እ—እባቡ፡ ሁለት እጥፍ ብልህ ነበር። ዘሩም ሁል ጊዜ በሁለት እጥፍ ብልሆች ናቸው። ዛሬ ግን ማይክራፎኑን በእጄ ይዤ እግሮቼን ፑልቢቱ ላይ ተክዬ፡ ወደ ፑልቢት ወጥቼ እንዲህ እናገራችኋለሁ። እነሆ፡ ዛሬ፡ እውቀታችሁ ወዴት አለ እላችኋለሁ? ወደዚያ ወርዶ ብዙ የአእምሯዊ እውቀት ያካበተው ፓስተራችሁ፡ ይነሣ፡ አገር ውስጥ ካሉ ሁሉ ይልቅ ትልቁ ቤተ ክርስትያን፡ ወዘተረፈ ፓስተር ነው። የእባቡ ዘር መኖርያው የት ነው? እንደነዚህ ባሉ ብልጥና ብልህ ሰፍራዎች፣ ብልሆች፣ አስተዋዮች ምሁራን። መኖርያው እነኚህ ናቸው። የሚኖረው በዚያ ውስጥ ነው።

273 "በመንፈሴ እንጂ፡ በኃይል እና በብርታት አይደለም፡ ይላል ጌታ።" አያችሁ? እዚህ ናችሁ...

274 አንድ ወጣት ወንድም አንድ ጥግ ላይ ቆሞ፡ አይኑ እስኪፈርጥ ድረስ እያለቀሰ፡ ምናልባትም ያረጀች ጊታሩን እየደረደረ፡ "ወንድሜ ሆይ፡ ና፡ ጌታን ተቀበል!" ሲል፡

275 አንድ ፓስተር፡ በአጠገቡ እያለፈ፦ "ኡህህ! የኔ ጉባኤ አይሆንም ነበር... እንዴት፡ ከዚህ ጋር ማበር አልፈልግም፡ እነ ሊዲ... እና እነ ጆኒ ሌሎቻቸው እንዲህ አይነት ሰፍራ እንዲያዩኝ አልፈልግም" ይላል። ሂድ፡ አንተ የዲያብሎስ ዘር፡ ወደ ዘለአለም ጥፋት ትሄዳለህ፡ አይቀርልህም። ትክክል ነው። ሌላ ቃል መናገር እችል ነበር፡ እላለሁም፡ "ዲቃላ ልጆች፡" አሁን የሚገኙበትም ይህ ነው። ምክንያቱ፡ አያችሁ፡ ከእናንተ...

276 "አባቴ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም። ወደ እኔ የሚመጣውን ሁሉ፡ በመጨረሻው ቀን አነሳለሁ። አንድም አይጠፋም። እይዘዋለሁ። እጠብቀዋለሁ። ከሱ በቀር፡ ይሄን ማድረግ የሚችል የለም።"

277 ሁሉ በእርሱ ነው። "ይህን አደረግሁ፡" ማለት አትችሉም። ይህን ሁሉ ያደረገው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ስለዚህ፡ እኔ ያደረግኩት የለም። የማደርገው በፍጹም አልነበረኝም፡ እናንተም፡ አልነበራችሁም። ምንም የማይገባችሁ ነበራችሁ። ሁሉንም ያደረገው እግዚአብሔር ነው። እናንተ አንድም ላይ ጣታችሁን መጠቆም አትችሉም። "እኔ፡ ከደህና ቤተሰብ ነኝ። **ይሄን** ያደረግኩ ነኝ፡" አትሉም። ፈጽሞ አይገናኝም። የእግዚአብሔር ምሕረት ነው፤ ያደረገውም እግዚአብሔር ነው።

278 አሁን ይቅርታ አድርጉልኝ፣ ገና አስራ አንድ ሰዓት አልሆነም፣ ለማንኛውም ግን እዘጋለሁ። አያችሁ?

279 መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ የሚናገረው እውነት መሆኑን ሰንቶች ይገባችኋል? በተለይ፡ የብራንሃም ተበርናክል ሰዎች። አሁን፡ ይህ ከትምህርታችን እና ከእምነታችን መካከል አንድ አስራ ሰድስተኛው ነው። ነገር ግን፣ ለእናንተ ተመልካቾች፣ እናንት እንደ አባል ወደዚህ የማትመጡ ሰዎች

ሆይ፡ እላችኋለሁ፡ እና አስታውሱ። እኛ የምናምንበት መንገድ፡ **ይህ** መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡ መጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔር እውነት ነው።

280 አሁን፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ፡ እንደነበረ፡ እኛ እንደምናምነው፡ እውነት እና እውነት ያልሆነውን ነገር የሚያውቁበት መንገድ ነበራቸው።

281 አሁን፣ የተጻፈ ሕግ እንደነበራቸው ሁላችንም እናውቃለን። ስንቶች ታውቃላችሁ? ሕግ፣ ትዕ—ትዕዛዛት ሁሉ፡ ታቦት ውስጥ፡ እና ሌላ ነገር ላይ ነበሩ፤ በጣም ጥሩ፡ ሕጉ ደግሞ ትእዛዛት ውስጥ ነበር። "አታመንዝር። ያመነዘረ ሁሉ በድንጋይ ይወገራል፡" ይላል። አያችሁ? ትእዛዙ እና፡ በትእዛዙ ላይ ያለውን ህግ ያ—ነበር። ታቦቱ፡ **እዚህ** ላይ ተቀምጦ ነበር፤ ትዕዛዛት ሁሉ በውስጡ ነበሩ፡ የትእዛዛት ሕጎችም በታቦቱ ውስጥ በጎን ነበሩ። አንድ ሰው ወርዶ፡ ቢያመንዝር፡ ደግሞም ከተያዘ ህጉ የሚለውን ታውቃላችሁ፡ "በድንጋይ ይወገራል።" ወደ ውጭ አውጥተው በድንጋይ ይወግሩታል። በትዕዛዛት የነበረ ሕግ ይህ ነበር።

282 አሁን ይህን የሚያውቁበት ሁለት መንገዶች ነበራቸው። ሁሉ፡ በሶስት ይጸናል። ሌላ የሚያውቁበት መንገድም ነበራቸው፡ እሱም በነብዪ ወይም በህልም ነበር። ስንቶች ታውቃላችሁ? "በመካከላችሁ መንፈሳዊ ሰው ወይም ነቢይ ቢኖር፡ እኔ እግዚአብሔር ራሴን በሕልም አሳየዋለሁ፡ በራእይም እናገረዋለሁ።" ትክክል ነው። እሱ፡ ትንቢት ተናጋሪ ነበር።

283 አሁን፡ አንድ ሰው መጥቶ፡ ይላል፡- "ኦህ፡ ሀሌ ሉያ፡ ተገልጦልኛል! በጌታ ስም ትንቢት እናገራለሁ። ተገልጦልኛል ሲል።" አሁን እናንተ እንደምታደርጉት፡ እንደዋዛ አይለቁትም። ከሁሉ በፊት፡ ነገሩን በእግዚአብሔር ይመረምሩታል።

284 በአሮን የደረት ኪስ ላይ፡ ኡሪም እና ቱሚም የሚሉት ነገር ነበራቸው። ይህን ቃል ስምታችሁ የምታውቁ ስንት ናችሁ? ምን ነበር? በሁለት ጎን ስድስት ስድስት ነበሩ ሆነው የተደረደሩ፡ የአሥራ ሁለቱ አባቶች አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች ናቸው፤ ኢያስጲድ፡ ለይሁዳ፣ እስከ ታች ድረስ፣ ለእያንዳንዳቸው፡ አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች። እና ነቢዪው፡ ወይም ህልም አላሚው ተይዞ፣ የደረት ኪስ ይሰቀላል፣ ሰውዬውም በዚያ ፊት ይቆማል። "አሁን ተንብይ ትንቢትን ተናገር፡" ይሉታል።

"እንዲህ—እንዲህ ይሆናል ጌታ በእርግጥ ተናግሮኛል።"

285 ፍጹም እውነት ሊመስል ይችላል፡ ምንም ያህል እውነተኛ ቢመስልም፡ የኡሪም እና ቱሚም፡ ብርሃኖች አንድ ላይ በርተው የቀስተ ደመና ሕብር ካልፈጠሩ፡ እነዚህ የተሰበሰቡ ብርሃናት፡ የመለኮታዊ ስራ፡ ምስክር ናቸው። አያችሁ፡ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለቃሉ ምስክር አለው። አያችሁ? እነዚያ መለኮታዊ መብራቶች ካላበሩ፡ ምንም ያህል እውነት ይምሰል አይገደኝም፡ ውሸት ነው።

286 ህልም አላሚው፡- "ሕልም አየሁ፤ ይህ ሕልም እንዲህ ይላል፡ ሕልሙም፡ 'ሶርያውያን መጥተው ይከብቧታልና፡ እስራኤል **በዚህ** በኩል እንዲህ ወደሚባል ስፍራ ተጓዙ ይላል።'" ህልም አላሚውን ይዘው ይወስዱትና፡ ህልሙን ይናገራል። እነኚያ መብራቶቹ ካላበሩ፡ ምንም ቢሆን፡ ተሳስቷል... ሶርያውያን በውግያ ማዶ ላይ ቀርበው ቢመጡም፡ ተሳስቷል። ኖ፡ ስር። ለእነሱ፡ የግድ፡ በኡሪም ቱሚም መረጋገጥ አለበት።

287 የጥንቱ የክህነት ስርዓት እንዳበቃለት፡ ኡሪም እና ቱሚምም፡ አብሮ እንደጠፋ ሁሉም ሰው ያውቃል። ያንን እናውቃለን፡ አይደል?

288 አዲስ የክህነት ስርዓት መጥቷል። ምን? ዛሬም ኡሪም እና ቱሚም አለንን? የስ፡ ሰር። ራሱ የእግዚአብሄር ቃል! የስ፡ ሰር። **ይህ** ነው። ማንም ምንም ዓይነት መገለጥ ካለው፡ ወይም አንዳች ነገር ቢናገር፡ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር-... ከቅዱሳን ቃላት ጋር የማይስማማ፡ የትኛውም ትምህርት ቢያመጣ፡ ተሳስቷል። የትኛውም የሐይማኖት ተቋም ይሁን፣ ምንም ያህል ይጎብዝ፣ ምንም ያህል ብልህ ይሁን፣ ምንም ያህል ይማር አይገደኝም፡ ተሳስቷል።

289 ሌላ አንድ ሰው መጥቶ፡ እኛ እዚህ ቤተክርስትያን ስለምንማራቸው ነገሮች፡ እንዲህ ብሎ፡ ቢነግራችሁ፡ "በውኃ ከተረጨህ፡ በቂ ነው፡" ቢላችሁ ዋሽቷችኋል። ይህ በኡሪም እና በቱሚም ላይ አይበራም። እንዲህ ብሎ፡ ቢነግራችሁ፡ "ውኃን ማፍሰስ፡ በቂ ነው፡" ቢላችሁ ዋሽቷችኋል። "'በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣' ሰም መጠመቅ ችግር የለውም፡" ብሎ ከነገራችሁ፡ ዋሽቷችኋል። "የተአምራት ዘመን አልፏል፡" ብሎ ከነገራችሁ፡ ዋሽቷችኋል። "ሴቶች መሰበክ ይችላሉ፡" ብሎ ከነገራችሁ፡ ዋሽቷችኋል። "በሐይማኖይ ተቋምህ ውስጥ ጸንተህ መቀጠል ችግር የለውም፡" ብሎ ከነገራችሁ፡ ዋሽቷችኋል። በኡሪም ቱሚም ላይ አይበራም። ከእሮጌቷ "እናት ጋለሞታ፡" የተፈለፈሉ ነገሮች እጅግ ብዙ ናቸው፡ ወደ ሁሉም ይወርዳሉ፡ ከሐይማኖት ተቋም የምንርቅበት ምክንያት ይህ ነው።

290 በየሐይማኖት ተቋማት ውስጥ ያሉ ወንድሞች እና እህቶች እንወዳቸዋለን። ይሁን እንጂ፡ "እኔ ሜቶዲስት ነኝ፡" ከእኔ ጋር፡ ክርስትያን ላድርግህ፡ አይባልም። ክርስቲያን የሆንከው በእግዚአብሔር መንፈስ ስለተወለድክ ነው። ሜቶዲስት ወይም ባፕቲሰት መሆን አገባህም። እንዳቸውም መሆን አይገባህም። በእግዚአብሔር መንፈስ መወለድ ብቻ ነው ያለብህ። ታምናላችሁ?

291 በዚህ መሠረት፡ ወደዚህ እምልኮ ኅብረት መግባት የሚፈልግ ማንም ሰው ካለ፣ እንዲሁም—በጥልቅ ውኃ ውስጥ፡ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም እጠመቃለሁ የሚል ሰው ካለ፡ ማጥመቂያ ተዘጋጅቷል። በአንድ ደቂቃ ውስጥ፡ ማጥመቅ ይጀምራሉ።

292 እንዲሁም፡ በሌላ ጉዳይ መምጣት የሚፈልግ፡ ወይም የምትፈልጉ፡ ሰዎች ካላችሁ? እነሆ አለን። ትክክል ነው።

293 አሁን፡ ወደ ቤተ—ክርሰቲያን እንዲሁ ትመጣላችሁ እንጂ፡ ምንም አባልነት የለንም። ክርሰቶሰ በሜቶዲስት ቤተ ክርሰቲያን፣ ባፕቲሰት ቤተ ክርሰቲያን፣ በፕሬስባይቴሪያን ቤተ ክርሰቲያን ውስጥ እንዳለ እናምናለን። በእያንዳንዳቸው አባላት አሉት። የጎደለው፡ ዛሬ፤ እነዚያን እያጋለጠ ያለው የሐሰት ትንቢት ነው፡ መጽሐፍ ቅዱስን የሚጻረር፡ የአብያተ ክርሰቲያናት ትምህርት ነው።

294 እንደው፡ ነገሩን የሚያብራራልኝ አንድ ሰው ባገኝ፡ እውነት እራሴን እፈትሻለሁ... መጽሐፍ ቅዱስ መርምሬ እራሴን ለማስተካከል የሚያስችለኝ፡ በውሰጤ በቂ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለኝ አምናለሁ። ጥላቻ እና ክፋት ገና በልቤ ውስጥ እያለ፡ ገና ቅናትና ክርክር እያለብኝ፡ አሁንም ኢየሱስ ክርሰቶስን ታላቅ ፈዋሽ እንደሆነ ሳላምን፡ እና ወዘተረፈ ከሆነ፡ በቃ ተነስቼ

ከሰባኪው ጋር ስለተጨባበጥኩ ብቻ፡ ስሜን በመፅሃፍ ላይ ከተመዘገበ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሰማማት፡ ፈጥኜ መሄድ አለብኝ። እንደማደርገው እርግጠኛ ነኝ። በዚህ ላይ—እውነት እናገራለሁ። ከእግዚአብሔር ጋር እሰማማለሁ። ባፕቲስት ወይም ሜቶዲስት በመሆኔ የጸናው ብሆን ኖሮ፡ ወርጄ ክርስትናን በልቤ ውስጥ አስገባው ነበር። አደርገዋለሁ። የሰ፡ ስር።

295 አሁን በመጪው እሮብ ምሽት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ የሚጀመረውን፡ መጪውን ሪቫይቫል አስታውሱ። በእነዚህ መሰረት ላይ ነው።

296 ወዳጆች ሆይ፣ ስሙ፣ እውነተኛና ሕያው አምላክ አለ። ትክክል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በቤተክርስቲያን አለ።

297 አሁን፣ የሆነ ሰው የነገረኝ ቢሆን፡ የመጠራጠር መብት ይኖረኝ ነበር። ነገር ግን፡ ስሙኝ። ከእለታት አንድ ቀን፡ ትንሽ ልጅ ሆኜ፡ ከዛፍ ስር ቆሜ፡ ያኔ አይቼዋለሁ። ሰምቼዋለሁ። ነገረኝ፡ እንዲህ አለኝ፦ “ከወራዳ ሴቶችን ራቅ። ከሲጋራዎች ራቅ። አንተ ስታድግ በአንተ የምሰራው ስራ አለኝና። ከመጠጥ፣ ከእርግማን፣ እና ከመሳሰሉ ነገሮች ራቅ ብሎኛል።” እሱ ቃሉን የሚጠብቅ፡ እውነተኛና ሕያው አምላክ እንደሆነ አውቃለሁ።

298 ትንሽ እንዳደግኩ፣ እንዴት እንዳገኘኝ፣ እንዴት እንዳናገረኝ! እሱን እንዴት እንዳየሁት፣ እንደሚነድ ቁጥቋጦ፣ ወዲያ ማዶ እንደሚንቀሳቀስ እሳት! እሱ ሲናገር የተናገረውን በትክክል ሲፈጸም እንዴት እንዳየሁት፤ እና፡ ሁል ጊዜ፡ ልክ እንደተናገረው ሙሉ ናቸው፡ እንዲሁ ሙሉ ናቸው።

299 እነዚያን የተሟሉ ነገሮችን እንዲሁ የሚናገረው፡ መጽሐፍ ቅዱስ እኔ በማስተምርበት መንገድ እንዳስተምር ያነሳሳኝ እርሱ ነው። ትክክል ነው። ስለዚህ፡ ወደ እኔ የመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እርሱም ትናንትናና፣ ዛሬ፣ ለዘላለምም ያው ነው።

300 ኢየሱስም፦ “እኔ ከአብ መጥቻለሁ፡ ወደ አብም እሄዳለሁ።” በመጣ ጊዜ...

301 ምድረ በዳ የነበረው አምላክ እርሱ፡ የሚነድ ብርሃን ነበር። ሰንቶች ታውቃላችሁ? እሱ የሚነድ ብርሃን፡ የእሳት አምድ ነበረ።

302 ወደዚህ ምድር መጣና፡ እንዲህ አለ፦ “ከአብ ወጥቼ መጥቻለሁ፡ እመለሳለሁ... ከእግዚአብሔር መጥቻለሁ፡ ወደ እግዚአብሔር እመለሳለሁ።”

303 ከሞተ፣ ከተቀበረ፣ ከተነሳ በኋላ፣ ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ሲያገኘው፡ ምን ነበር? አሁንም የእሳት አምድ ነበር። የሰ፡ ስር።

304 በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ምን አደረገ? ጳውሎስን ሲያገኘው ምን አደረገ? እንዴትስ ላከው? እንዴት እንደሚጠመቅ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት ወደሚነግረው ነብዩ ላከው፤ እጁንም ጭኖ ፈወሰው፡ ራእይም እንዳየ ነገረው።

305 ዛሬም ይህ ኢየሱስ፡ ተመሳሳይ ነገሮች እያደረገ፣ ተመሳሳይ ትምህርት እያስተማረ፣ በገዛ ቃሉ እና በምልክቶች እና በድንቆች እያረጋገጠ፣ አሁን ያው የእሳቱ አምድ ነው። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፡ እንኳን ክርስቲያን ሆንኩ። እንኳን ክርስቲያንኖች ሆናችሁ።

306 ለእናንተ፡ ለዚህ ተበርናክል፡ ሰሙን እንቀይረዋለን ብየ ነግሬአቹአለሁ። ብራንሃም ተበርናክል ተብሎ መጠራቱ ልክክ አይደለም። ሰው ነውና፡ አያችሁ። ሰሙን እንቀይረዋለን፡ ሌላ ሰያሜ እንሰጠዋለን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እንገባበታለን። እኔ የሕያው—የእግዚአብሔር ቤተ ክርሰትያን እንዲሆን እፈልጋለሁ። ሜቶዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕሪስባይቴሪያን፣ ጴንጤቆስጤ አልፈልግም። እ...

307 እነዚህ ሁሉ ሰዎች፣ በሙሉ ልቤ እወዳለሁ። የትኛው ማን እንደሆነ አላውቅም። እከሌ ነው ማለት አልችልም። ቃሉን ብቻ እሰብካለሁ። መረቤን ጥዬ መጎተት ነው። እንቁራሪቶች፣ የውሃ ሸረሪቶች፣ እና እባቦች ይኖራሉ፡ አንዳንድ ዓሦችም አሉ። ያንን የሚወሰነው እግዚአብሔር ነው። መረቡን ጎትቼ፣ ቃሉን ብቻ ሰብኬ በመጎተት፣ እንዲህ እላለሁ፦ "እነሆ፣ ጌታ ሆይ፣ በመሠዊያው ዙሪያ ናቸው። የአንተ የሆኑትን ታውቃለህ፡ ከመሠረቱ ጀምረህ ታውቃቸዋለህና። እኔ ማድረግ የምችለው ይህ ነው። የትኛው ማን እንደሆነ አላውቅም። ጌታ ሆይ፡ አንተ ታውቃለህ፡ አንተው አድርገው። ወደ ሌላ ቦታ እመለከታለሁ፣ እና ሌሎች ቡድን አስገባለሁ። ማድረግ የምችለው ያ ብቻ ነው።" በጣም ጥሩ።

> ኦህ፣ ተጓዝ ተጓዝ ያሰኘኛል፡
> ተጓዝ ተጓዝ ያሰኘኛል፤
> የሰማይ ቤቴ ውብ እና ድንቅ ነው፣
> ተጓዝ ተጓዝ ያሰኘኛል።

308 አሁን አስታውሱ፡ ቀጠሮ ማስያዝ የምትፈልጉ ሰዎች፡ ሚስተር፡ መርሴርን፡ በ BUtler 2-1519 ደውሉለት። [ስልክ ቁጥሩ ተቀይሯል—አርታዒ።] እናንተን ማግኘት ደስታችን ነው። የምትወዳቸው ሰዎች ከመጡ፣ በሪቫይቫሉ ጊዜ መቸኮል አለብን... አሁን እሄዳለሁ፡ ከዛሬ ምሽት ጀምሮ፡ ለራሴ ጊዜ እሰጣለሁ፡ ለሁለት ቀናት እሄዳለሁ፡ ለራሴ ጊዜ እሰጣለሁ።

309 እዚያ ገብቼ እንደዚህ፡ ወደ ጥናት እወጣለሁ፣ "ጌታ ሆይ፣ አጠገቤ ነህ። እዚህ እንዳለህ አውቃለሁ።ወደ አንተም ወደሚቀርቡት ትቀርብ ዘንድ ቃልህ ተናግሯል።" የእሳት ዓምድ ሲንቀሳቀስ ማየት እስክችል ድረስ መጸለይና መመልከቴን እቀጥላለሁ። ያኔ ዝግጁ እንደሆነ አውቃለሁ። ያኔ ለፈውስ አገልግሎት፣ ለጸሎት፣ የታመሙ እና የተጎዱትን ለመርዳት የምችለውን ለማድረግ ወደ መድረኩ እወጣለሁ።

310 ስለ መልካምነታችሁ ሁላችሁም እናመሰግናለን። ስትመጡ፡ አምናችሁ ኑ፡ ታላቅ ጉባኤ እንዲኖረን እንጠብቃለን። ይህ ማለት እፈልጋለሁ...

311 ወንድም ጄፍሪስ፣ ዛሬ ማታ እዚህ አለ? ወንድም ጄፍሪስን ስለ ስራው ማመስገን እንፈልጋለን። ወደ ደሴቶች እና ወዘተ፡ ተመልሶ እንደሄደ እገምታለሁ።

312 ወንድም እና እህት ራይትን፣ እና ብዙዎቻችሁ እዚህ በማየቴ ደስ ብሎኛል።

313 እና ጠበቃው ሮበርትሰን፣ ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሲገባ አይቼዋለሁ። ስለ በቀደም ለታ—ስለ መልእክቱ ላመሰግነው እወዳለሁ። ማን እንደሆነ ማንም አልተናገረም። ያ ያሳፍራል። ዛሬ ማታ እንደምሰብከው ያለ፡ በትንቢት እውነተኛና ጥሩ መልእክት አስተላልፏል።

314 ከዛ በኋላም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ወይም ትላንት ማታ ከሜቶዲስት ቤተ ክርስትያን ሌላ አገልጋይም ነበር፡ ወንድም ሰሚዝ... ወይስ እዚያ፡ ከቸርች ኦፍ ጋድ ነው። ዛሬ ማታ፡ እዚህ ይኑር አይኑር አላወቅኩም። በዚህ መድረክ ላይ ቆማችሁ ወደዛ ወደ ኋላ ሰታዩ፣ ሜዳ ሰለሆነ፡ ለመናገር ይከብዳል፡ አያችሁ፡ አይታወቅም። ወንድም ሰሚዝ፡ እዚህ ካለህ፡ እናመሰግናለን።

315 እዛ ከኋላ፡ ከወንድም ኮሊንስ አጠገብ፡ የተቀመተው ወጣት፡ ከጆርጂያ የመጣው ወንድማችን አይደል? [ወንድም ነቪሌ፡ "አዎን" አለ።—አርታዒ።] ዛሬ ማታም በድጋሚ እዚህ አንተን በማየቴ ደስ ብሎኛል ወንድሜ።

316 ሌሎቻችሁም፡ ሁላችሁም፡ አንዱ ሌላውን ትተዋወቃላችሁ።

317 እቺ እህት እና ያ ወንድም ለህጻኗ ለመጸለይ የሄዱ ሰዎች ናቸው መሰለኝ፡ እዛ ጋር፡ አተገባቸው ዶክተሩ ተቀምጧል። ጌታ ይባርክህ፡ ዶክተር።

318 አሁንም፡ አገልጋዮች እና ወንድሞች ሆይ፣ ነገሩን በኃይል ጠበቅ ማድረጌ፡ ከረር አድርጌ በማሰሬ ምክንያት እባካችሁ በእኔ ላይ ቅር አይበላችሁ። ይህ ቤተ ክርስትያናችን ነው። የቆምንለት ዓላማ ይህ ነው፡ ቃሉን ላይ በትክክል እያስቀመጥን፡ ልንቀሰቅሳቸው እንወዳለን። ምናልባት፡ ከመሰመር ከወጣችሁ፡ ተመልሰን መጥተን እንዲህ እንላችኋለን፦ "የተሻለ ታውቃለህ። ቴፑ ላይ አለልህ።" አያችሁ? ይኸው። "ቴፑ ላይ አለላችሁ።"

319 መሄድ ከሚገባን በላይ አብዝተን ሄደናል፡ ሌዮ። ይሁን እንጂ፡ እኛም... እናንተም ብዙ አግኝተናል። እጥብቃችሁ ያዙት፡ ሌላው ከጥቂት ጊዜ በኋላ እናገኘዋለን። ሰውዬው ሀብሐብ እየበላ፡ "በጣም ጥሩ ነው፡ ገና የቀሩ ነገሮች አሉ እንጂ፡" እንዳለው ነው። ሰለዚህ እኛም ብዙ ተጠቅመናል፡ ሌላም፡ እየመጣ ነው።

320 ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ። አሁን ሁላችንም... የጥምቀት ሰነ ሰርዓት ይኖረናል። ልክ ነው፡ ወንድም ነቪሌ? [ወንድም ኔቪል "አዎን፡ ይመስለኛል" አለ።—አርታዒ።] አሁን መጠመቅ የሚፈልግ ሰው አለ? ማንነትህ እያስጨንቀንም፡ ለማጥመቅ—ተዘጋጅተናል። ልትጠመቁ ተዘጋጅታችሁ የነበራችሁ፡ እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሱ። የሆነ ሰው፡ እዛጋ... አንድ እመቤት አለች ይመስለኛል። ሌላ ሰው አለ? ሌላው፡ ለወንዶቹም ለሴቶቹም ልብሶች አዘጋጅተናል።

321 እንግዲህ፡ "ከባፕቲስት ቤተ ክርስትያንን ውጡ። ከሜቶዲስት ቤተ ክርስትያን ውጡ፡" እያልናችሁ አይደለንም። አንልም። ወደ ቤተ ክርሰቲያናችሁ ተመለሱ። ነገር ግን መጽሐፍ እንደሚል፡ በጌታ በኢየሱስ ሰም ካልተጠመቃችሁ ግን... በ "ኢየሱስ" ሰም ብቻም፡ አይደለም። በ "ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ" ሰም፡ ቃሉም ይህ ነውና። ጥምቀታችሁ ሰህተት ነው።

322 ወደ ወንዙ ሰደርስ ምንም እንከን አልፈልግም። ጊዜው ሰደርስ በጊዜ መብረር ሰለምፈልግ፡ ትኬቴን በእጄ ይዤ፡ አያችሁ፡ የማውቀውን ሁሉ ያህል ንጹህ አድርጌ ማቆየት እፈልጋለሁ። እናንተም እንዲህ እንድታደርጉ እመክራችኋለሁ።

323 ወደ ቤተ ክርስትያናችሁ ተመለሱ። ይህ በእናንተ፡ እና በእግዚአብሄር መካከል ነው። እኔ ማለት የምችለው ግን ይህ ነው።

324 በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ግን “በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” ስም በቀር በሌላ መንገድ የተጠመቀ ማንም የለም። የተጠመቁትንም፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ እንዲህ ብሎ አዘዛቸው፡ “የሰማይ መልአክ ሌላ ነገር ቢሰብካችሁ፡ የተረገመ ይሁን።” መጥተው “በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ” ስም፡ እንደገና፡ እንዲጠመቁ አዘዛቸው። ትክክል ነው። እንዲሁም አደረገ። እርሱ እንዳደረገ፡ እኛም እናደርግ ዘንድ አዘዘን፡ የምናደርገውም፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

እግር በመተጣጠብ እናምናለን። በጌታ እራት እናምናለን።

325 በክርስቶስ ዳግም ምጽአት፡ በሚታየው ሰውነቱ፡ ጌታ በመዓርግ አካሉ እንደሚመጣ እናምናለን፤ በመንፈስ ሳይሆን፡ ኢየሱስ በመዓርክ አካሉ በክብር ይመጣል።

326 በሥጋዊ የአካል ትንሣኤ እናምናለን፣ ወደ መቃብር ስንወርድ፡ በወጣትነት በረከት ለዘለአለም የሚኖር፡ አዲስ አካል እንጂ፡ ያረጀና፡ የተሸበሸበ አካል እንቀበልም።

327 በነፍስ ፍፁም አለመሞት እናምናለን። አንድ የዘላለም ሕይወት ብቻ እንዳለ እናምናለን፡ ይህም ከክርስቶስ ኢየሱስ የሚገኝ ሕይወት ነው። በትክክል እውነት ነው።

328 ስለዚህ፡ ዘላለማዊ ቅጣት አለ ብለን እናምንም። ድኝ የሚቃጠልበት፡ ገሃነም እሳት መኖር እናምናለን፡ ይሁን እንጂ ለዘላለም ይቃጠላል ብለን እናምንም፡ እንዲህ ከሆነ′ማ፡ የዘላለም ሕይወት አገኙ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚገኝ፡ አንድ የዘለአለም ህይወት አለ። ይህ እውነት ነው። ምናልባት አንድ ሚሊዮን፡ አሰር ሚልዮን ዓመታት ትቃጠላላችሁ፡ እኔ አላውቅም፡ የዘላለም ሕይወት ማግኘት ግን አትችሉም። ለዘለአለም አትቃጠሉም… ለዓመታት ትቃጠላላችሁ እንጂ፡ ለዘለአለም አይደለም። አያችሁ፡ በኢተርናል እና በፎርኤቨር መካከል ልዩነት አለ። **ፎርኤቨር** ከዓመት እስከ ዓመታት ማለት ነው፡ እስከ፡ ማለት “የጊዜ ገደብ ነው።” ዘላለማዊነት፡ ግን፡ ዘላለማዊ ቅጣት የለውም።

329 አንድ ብቻ የዘለአለም ህይወት ሰላለ፡ የዘለአለም ህይወት አላችሁ። የዘላለም ሕይወት ያለው ደግሞ፡ ሕያው ሆኖ በእግዚአብሔር ተባርኮ ይኖራል።

330 “ነገር ግን ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ፡ ያቺ ነፍስ… ” ምንድን? [ጉባኤው “ትሙት” አለ።—አርታዒ።] ትክክል ነው። ስለዚህ፡ የዘለአለም ህይወት አታገኝም። በትክክል። የቅጣት ጊዜ አለው—ይሁን እንጂ፡ ዘለአለማዊ አይደለም።

331 ስለዚህ፡ እንዳያችሁት፡ ብዙ የምንማራቸው ነገሮች አሉ፡ ሌላ ቀን እንመለሰበታለን። ጌታ ይባርካችሁ።

332 እህታችን እየመጣች ሳለ፡ ይህን ጥሩ የድሮ መዝሙር እንዘምር። ያቺ እመቤት ትኖራለች ብዬ አምናለሁ…

333 ሮዜላ፡ እሷ እናትሽ ናት? [እህት ሮዜላ “አዎን፡” አለች።—አርታዒ።] በይ፡ ልብሽን ይባርክ! እህቴ፡ ይህን ስታደርጊ በማየቴ፡ ደስ ብሎኛል። በጣም ጥሩ ነው።

334 አሉን ከምንላቸው መልካም ወዳጆች አንዷ፡ ሮዜላ ግሪፊን ናት። ምናልባት እንግዶች ለሆናችሁ፡ እሷንም ለማታውቋት፡ የአልኮል ሱሰኛ የነበረች ወጣት ሴት ናት። ሮዜላ እንዲህ በማለቴ ምንም አይመስላትም። ያኔ እዛ… መድረክ ላይ ስትወጣ—ኢንዲያና ውስጥ ነበር። ጎሰቋላ ሰው አይታችሁ ካወቃችሁ፡ ባለ ድፍርስ አይን የአልኮል ሱሰኛ፡ እሷ ነበረች። አዎን፡ አራት የቺካጎ ዶክተሮች… ሰም አልባ የአልኮል ሱሰኛ፡ እና ሌላ ሌላ ነገር ናት ብለው፡ ፈርጀዋታል። ነገር ግን አንድ ቀን ምሽት ወደ ጉባኤው ስትገባ፡ መንፈስ ቅዱስ ሕይወቷን ገልጦ ነገራት። ያኔ አበቃለት።

335 አሁን ተመልከቷት፡ ከሰላሣ-በላይ እገምታታለሁ፡ ወደ አሥራ ሰምንት ዓመት፡ ቆንጆ፡ ዉብ ወጣት ሴት ተሸጋግራለች። ከዚያ ጊዜ በኋላ ዊስኪ ቀምሳ አታውቅም፡ አምሯትም አያውቅም። ለለክርስቶስ በመኖር፡ በየጎዳናው እየወጣች፡ ለሐጢ አተኞች እና ለሰካራሞች፡ ስለ እግዚአብሔር ክብር ትመሰክራለች፡ በቺካጎ ዙርያ፡ ባሉ የሰካራም መንደሮች፡ እና በተለያዩ ቦታዎች፡ ስለ ጌታ የሆነ ነገር ታደርጋለች።

336 በጌታ በኢየሱስ ሰም ተጠመቀች፡ እናቷም እንዲሁ ለመጠመቅ ዛሬ ማታ መጣች፤ እግዚአብሔር ቢፈውሳት፡ ኢየሱስ ቢፈውሳት… "በቃልም ሆነ በሰራ የምታደርጉትን ሁሉ፡ በማን ሰም አድርጉት… " [ጉባኤው "በኢየሱስ ክርስቶስ፡" ሰም አለ።—አርታዒ።] መጽሐፍ ቅዱስ ያለው ይህ ነው። ትክክል ነው።

337 እሺ፡ አሁን የጥምቀት ሰነ ሰርዓት እናካሂዳለን። ለአገልግሎት ሰንዘጋጅ፡ ለመጠመቅ ለጥቂት ደቂቃዎች መብራቱን ወደ ውጭ እናወጣለን፡ ከዛም—በጌታ ዘንድ መልካም ጊዜ እንጠብቃለን።

338 ዛሬ ማታ የጥምቀት ሰርዓት ታከናውናላችሁ? እሺ መልካም፡ ብትዘጋጁ—ይሻልሃል። ሌሎቻችን ሰንዘጋጅ፡ እኔ መዝሙር ሌላ ሌላ፡መምራት እጀምራለሁ። እሰኪዘጋጁ ድረስ… [ወንድም ኔቪል እንዲህ "ዶክ፡ እዚህ ልብሶች አሉ? " አለ፤—አርታዒ።] ዶክ፡ በፍጥነት፡ የጥምቀት ልብሶች። በጣም ጥሩ።

339 ከእነዚህ የጥንት… ጥሩ መዝሙሮች አንዱን እንዘምር [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

340 ይህን እሰክናደርግ ድረሰ፣ ሁላችንም እየወጣን፡ ምን እናድርግ?

> አንተም የየሱስ ሰም ተቀበል፡
> በእግሩ ስር ውደቅ፡
> የነገስታት ንጉስ፡ ይንገስ በሰማይ፡
> ጉዟችን ሲጠናቀቅ።

እሺ፡ በእግሮቻችን እንቁም።

> የሀዘንና የዋይታ ልጆች ሆይ፡
> የኢየሱስን ሰም ተቀበሉ፡
> ደሰታ እና ምቾት ይሰጥዎታል፣

341 ምን እንደምናደርግ እነግራችኋለሁ። ወደ ቀኝ ዞር በሉና አጠገባችሁ ካለ ሰው ጋር ተጨባበጡ፡ እንዲህም በሉት፡- “እንዴት ነህ ወንድሜ? በእውነት አብሬህ በዚህ ጉባኤ ከአንተ ጋር በመገኘቴ ደስተኛ ነኝ።”

ውድ ስም፣ ኦ ድንቅ ነው!
… የሰማይ ደስታ፤
ድንቅ ስም፡ ኦ… (ውብ ስም!)

**የእባቡ ዘር** AMH58-0928E

(The Serpent's Seed)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሁድ ማታ፡ መሰከረም 28፡ 1958 በዩ.ኤስ.ኤ፡ ጀፈርሰንቪለ ኢንዲያና፡ በሚገኘው ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጒሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org